በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግስት

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር

## የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማነትን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማውጫ


ማውጫ ......................................................................................i
**የክዋኔ ኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ማጠቃለያ**..............1
**ክፍል አንድ** ..................................................................................3
መግቢያ ..........................................................................................3
የሚኒስቴር መ/ቤቱ አመሰራረት ...............................................................3
የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይና ተልዕኮ ...........................................................5
የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፖሊሲ ዋና ዋና ዓላማዎች...........................................5
የሚኒስትር መ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር.........................................................6
የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር አደረጃጀት እና የሰው ኃይል ...............................7
የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ.......................................................8
የኦዲቱ ዓላማ....................................................................................8
የኦዲት አከባቢ (Potential Audit Area) ....................................................8
የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ..............................................8
የኦዲት መመዘኛ መስፈርት.....................................................................9
የኦዲቱ ወሰን......................................................................................9
የኦዲቱ ዘዴ .......................................................................................9
የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት ትኩረት መስክ ስዕላዊ መግለጫ /System Description/..................................i
**ክፍል ሁለት** ...................................................................................12
**የኦዲት ግኝቶች**.................................................................................12
2.1. ቴክኖሎጂዎችን የማፈላለግ፣ የመምረጥ እና የማስገባት ስራዎች አፈፃፀም ወጪ ቆጣቢና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፣ ..........................................................................................12
ቴክኖሎጂዎችን ለማፈላለግ፣ ለመምረጥ እና ለማስገባት የሚያስችል አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች መውጣታቸውንና ተግባራዊ መደረጋቸውን በተመለከተ፣ ............................................12
ቴክኖሎጂን ለማሸጋገር ለሚሰሩ የምርምር ፕሮግራሞችን ድጋፍ መደረጉን በተመለከተ፣ ........................13
የሀገሪቱን የቴክኖሎጂ ፍላጎትና ክፍተት መሰረት ያደረገና ሊሸጋገሩ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን በጥናት ላይ ተመስርቶ ያፈላለገ መሆኑን በተመለከተ፣ ...............................................................15
በየዘርፉ የሚሸጋገሩ ቴክኖሎጂዎችን አመራረጥን በተመለከተ፣ ...............................................17
በቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት ዙሪያ የሚከሰቱ ክፍተቶች ከሚመለከታቸው አካላትጋር በመሆን የሚገመገሙ መሆኑን በተመለከተ፣..........................................................................19
2.2 ቴክኖሎጂዎችን የማላመድ፣ የመጠቀም እና የማስወገድ ስራዎችን አፈፃፀም ወጪ ቆጣቢና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ ..........................................................................................20
ቴክኖሎጂዎችን ለማፈላለግ፣ ለማላመድና ለመጠቀም የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠቱን በተመለከተ፣ ..........................................................................................20

ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ቴክኖሎጂዎች በተለያዩ የማስታወቂያ ዘዴዎች ለህብረተሰቡ የሚተዋወቁ ስለመሆኑ፣ ....................22

አገልግሎት የማይሰጡ ቴክኖሎጂዎች የሚወገዱበት ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፣ ....................23

የቴክኖሎጂዎችን በአግባቡ ለማሸጋገር ሀገራዊ የቴክኖሎጂ አቅም መፍጠር የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፣....................25

ችግር ፈቺ ተብለው የሚከናወኑ ምርምሮች ወደ ተግባር የሚሸጋገሩ መሆኑን በተመለከተ፣ ....................27

2.3. በቴክኖሎጂ የተደገፈ መረጃ አያያዝ እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩን በተመለከተ....................28

የቴክኖሎጂ መረጃ አያያዝ እና ሥርጭትን ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣....................28

የቴክኖሎጂ ፍላጎትን ለመዳሰስ፣ ለማፈላለግ፣ ለመምረጥ፣ ለማስገባት፣ ለመቀመር፣ ለመጠቀምና ለማስወገድ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፣ ....................30

አገር በቀል የቴክኖሎጂ መረጃዎች በሚኒስቴር መ/ቤቱ ድረ-ገፅ ላይ መቀመጣቸውን በተመለከተ፣ ....................31

የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት አገልግሎት የሚሠጡ ተቋማት በክልሎች መቋቋማቸውን በተመለከተ፣ ....................32

**ክፍል ሶስት**....................34

**መደምደሚያ**....................34

**ክፍል አራት**....................36

**የማሻሻያ ሀሳቦች**....................36

**አባሪ 1፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶችና ዘዴዎች**....................39

**አባሪ 2፡ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር አደረጃጀት**....................44

# የክዋኔ ኦዲቱ ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ማጠቃለያ

(Executive Summery)

በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ በኦዲቱ ወቅት መረጃዎችን በመከለስ እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ኃላፊዎች ቃለ መጠይቅ በማድረግ ከዚህ በታች የታዩትን ዋና ዋና ግኝቶች እና የተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦችን ታይተዋል፡፡

- ቴክኖሎጂን ለማፈላለግ ለመምረጥ፣ ወደ አገር ውስጥ ለማስገባትና ለመጠቀም የሚረዳ ረቂቅ ደንብ በ2005 ዓ.ም በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጀ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልጸደቀ መሆኑ፣
- በ20 የተለያዩ ዘርፎች ላይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በጥናት ላይ ተመስርቶ የቴክኖሎጂ ፍኖተ ካርታ ሰነዶች ያዘጋጁ ቢሆንም ለተጠቃሚዎች ለማሰራጨት የህትመት ዝግጅታቸው ያልተጠናቀቀ በመሆኑ ያልተሰራጩ መሆኑ፣
- ወደ አገር ውስጥ በየዘርፉ የሚገቡ ቴክኖሎጂን ለመምረጥ የሚያስችል የመምረጫ መስፈርት ያልተዘጋጀ በመሆኑ በየዘርፉ ያሉ አስተባባሪዎችና ፈጻሚዎች ያለ መምረጫ መስፈርት ቴክኖሎጂዎች እየመረጡ ወደ አገር ውስጥ እያስገቡ መሆናቸው፣
- የጨረር አገልግሎት ሰጥተው የተበላሹ እቃዎችን በኢትዮጵያ ጨረር መከላከያ እንዲወገዱ የሚደረግበት ሁኔታ ከመኖሩ ውጭ በናሙና ተመርጠው በታዩ ዩኒቨርሲቲዎች፣ በመካከለኛና ከፍተኛ ማምረቻና አገልግሎት መስጫ ተቋማት እና በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ተቋማት ውስጥ የሚገኙ አገልግሎት የማይሰጡ ቴክኖሎጂዎችና ተጓዳኝ ዕቃዎች በሚኒስቴር መ/ቤቱ የማይታወቁ መሆኑ፣ በባለሙያ ተረጋግጠውና ተለይተው የሚወገዱበት ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፣
- ቴክኖሎጂን በማሸጋገር ሀገራዊ የቴክኖሎጂ አቅም ለመፍጠር እንዲቻል ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ2006 ዓ.ም የትምህርትና ስልጠና፣ የምርምር ተቋማት እና የኢንዱስትሪ ትስስር አሰራር የተዘጋጀ ቢሆንም 17 የቀጠና ፎረም አስተባባሪዎች ከመመስረትና በትስስሩ የሚሳተፉ ባለድርሻ አካላት ትውውቅ ከመከናወኑ ባለፈ በትስስሩ የተከናወኑ ተግባራት ላይ ውስንነት መኖሩ፣
- ችግር ፈቺ ተብለው ለሚከናወኑ ምርምሮች በሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚደረግ የገንዘብ ድጋፍ የተከናወኑ ምርምሮች ወደ ተግባር የሚሸጋገሩበት ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፣
- በምርምር የተደረሰባቸውና ወይም የተቀዱ ቴክኖሎጂዎች ወደ ምርትና ምርታማነት ያልተቀየሩ መሆኑ፣
- የቴክኖሎጂ ማበልፀጊያ ማዕከላት አለመቋቋማቸው ታውቋል፡፡

በመሆኑም

- በረቂቅ ደረጃ የሚገኘው ቴክኖሎጂን ለማፈላለግ፣ ለመምረጥ፣ ለማስገባት፣ ለመጠቀም፣ ለማላመድና ለማስወገድ በ2005 ዓ.ም. የተዘጋጀው ደንብ የወቅቱን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ተከልሶ እና በባለድርሻ አካላት ተገምግሞ

በአስቸኳይ በሚመለከተው አካል ጸድቆ ተግባራዊ በማድረግ ወደ ትግበራ ሊሸጋገር ይገባል፡፡ በተጨማሪ ደንቡን ለማስፈፀም የሚረዱ መመሪያዎች ሊዘጋጁና ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡

- የተዘጋጁት የፍኖተ ካርታ ሰነዶች በሙሉ የአርትኦት ሥራቸው እና ህትመታቸውን በማጠናቀቅ እና ለሚመለከታቸው አካላት በማሰራጨት ወደ ተግባር እንዲገቡ ሊደርግ እና አፈጻጸሙም ላይ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- በሀገር ውስጥ የሚገቡ ቴክኖሎጂዎችን ለመምረጥ የሚያስችል ለየዘርፉ የሚያገለግል የመምረጫ መስፈርት ሊዘጋጅና በተዘጋጀው መምረጫ መስፈርት መሰረት ቴክኖሎጂዎችን የሚመርጥ ለየዘርፉ ኮሚቴ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በማቋቋም ቴክኖሎጂዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ በማድረግ ሽግግሩ እንዲከናወን የሚደረግበትን አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ለቴክኖሎጂ ሽግግር ወደ አገር ውስጥ ገብተው ጥቅም ላይ ሳይውሉ ወይንም በሥራ ላይ ተበላሽተው ያሉ ቴክኖሎጂዎችና ተጓዳኝ ዕቃዎች በባለሙያ ተረጋግጠውና ተለይተው ሰው፣ እንስሳትና አካባቢን በማይጎዱ መልኩ የሚከማቹበት እና የሚወገዱበት ሥርዓት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ቴክኖሎጂዎችን በአግባቡ ለማሸጋገር ሀገራዊ የቴክኖሎጂ አቅም መፍጠር ለማስቻል የተዘረጋው የትምህርት ስልጠና፣ የምርምር ተቋማት እና የኢንዱስትሪ ትስስር ለመፍጠር የተዘረጋው ስርዓት ተግባራዊነቱ ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በጥልቀት ሊፈትሽና የመፍትሔ አቅጣጫ ሊያስቀምጥ ይገባል፡፡
- ችግር ፈቺ ተብለው ከፍተኛ ወጪ ወጥቶባቸው የሚከናወኑ የምርምር ሥራዎች ወደ ተግባር የሚሸጋገሩበት ስርዓት በመዘርጋትና ተግባር ላይ እንዲወጡና ሥራ ላይ እንዲውሉ በማድረግ ለምርምሩ መነሻ የነበሩት ችግሮች የሚፈቱበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡ በተጨማሪም በምርምር የተደረሰባቸው፣ የፈለቁ ወይም የተቀዱ/ኮፒ የተደረጉ/ ቴክኖሎጂዎች ወደ ምርትና ምርታማነት ለመቀየር የሚያችሉ የቴክኖሎጂ ማበልፀጊያ ማዕከላትን በማቋቋም ምርምሮቹ ወደ ተግባር ተቀይረው ለባለድርሻ አካላት እና ለተጠቃሚዎች የሚሰራጩበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

በማለት የማሻሻያ ሃሳቦች ሰጥተናል፡፡

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. የኢኮኖሚ እድገትን ቀጣይነት ለማረገገጥ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግሩን ውጤታማ ለማድረግ ጠንካራ ሀገራዊ የቴክኖሎጂ አቅም መገንባት እንደሚያስፈልግ በኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂው ተቀምጧል፡፡ በመሆኑም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶበት እየተሰራ ይገኛል፡፡

2. ኢትዮጵያ ቴክኖሎጂን የማፍለቅ እና የመጠቀም አቅሟ አናሳ ቢሆንም ታሪክ ግን ቀድማ ቴክኖሎጂን መጠቀም እንደጀመረች ያሳያል፡፡ ይኸውም የሰው ቅሪት አካል የምርምር ውጤቶች እንደ አረጋገጡት ከሆነ ኢትዮጵያ የሰው ዘር መገኛ ሀገር ናት፡፡ የሰው ልጅ የቴክኖሎጂ ታሪክ የሚጀመረውም መሣሪያዎችን ለመሥራት ተስማሚ የሆነውን የድንጋይ ዓይነት ከመምረጥና ድንጋዩ በሁለቱም ጎን ስለት እንዲኖረው ማድረግ ከመቻል ነው፡፡ በመሆኑም 1.6 ሚሊዮን እስከ 300,000 ዓመት በፊት የኖረው ሆሞ ኢሬክተስ (Homo erectus) የተባለ የሰው ልጅ ዝርያ በሀገራችን የስምጥ ሸለቆ ይኖር እንደነበር በዘርፉ የተደረጉ ጥናቶች ውጤት ያሳያል፡፡ በዘመኑ ይኖሩ የነበሩ ሰዎችም አኗኗር በአደንና ቅጠላ ቅጠል፣ ፍራፍሬና ሥራሥር በመልቀም ላይ የተመሰረተ በመሆኑ መሣሪያዎችን በመስራት ራሳቸውን ከአውሬ ለመጠበቅ፣ ማደሪያ ቦታቸውን ለመስራት፣ ለአደንና የዕፅዋት ሥራ ሥርን ቆፍሮ ለማውጣትና ሌሎች ተግባራትን ለማከናወን ይጠቀሙባቸው ነበር፡፡ በመሆኑም ሀገራችን የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ቀድማ ትጠቀም ነበር፡፡ በተጨማሪም ሀገራችን የምህንድስና፣ የባዮ ቴክኖሎጂ እና በሀገር በቀል የህክምና ዕውቀት ልምድ እንደነበራት የሚታወቅ ነው፡፡

3. ነገር ግን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ አለም የደረሰበትን የዕድገት ደረጃ ስንመለከት ሀገራች ያለችበት ደረጃ ለንፅፅር የሚቀርብ አይደለም፡፡ በመሆኑም መንግስት የአለምን ሁኔታ በመገንዘብ ኢኮኖሚያዊ ቴክኖሎጂ እድገት እና አዝማሚያ የሚከተል ስርዓት በመዘርጋት ለቀጣይ የቴክኖሎጂ እድገት ወሳኝ ሚና የሚኖራቸውን ዘርፎች በመለየት ለውጥ ለማምጣት ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ አመሰራረት

4. በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ጉዳዮችን የሚያስተባብርና የሚመራ የመንግስት አካል ለመጀመሪያ ጊዜ የተቋቋመው በ1968 ዓ.ም. በአዋጅ ቁጥር ቁጥር

62/1968 የኢትዮጵያ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን በሚል ነበር፡፡ በወቅቱ የኮሚሽኑ ዓብይ አላማው የነበረው የሀገሪቱን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ውጤቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ የሳይንስና ቴክኖሎጂ እንቅስቃሴዎችን አቅጣጫ መቀየስ የሚጕለብቱበትን ስልት መንደፍና ማበረታታት እንዲሁም ሳይንስና ቴክኖሎጂ በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ መንግስትን ማማከር ነው፡፡

5. በ1987 በአዋጅ ቁጥር 91/1987 በድጋሚ ሳይንስና ቴክኖሎጂ በኮሚሽን ደረጃ ተቋቁሟል፡፡ በዚህም ወቅት ከሰነድ ስራዎች በዘለለ ወደ ተግባር ስራዎች መግባት የጀመረበት ወቅት ነበር፡፡ ኮሚሽኑ የተለያዩ ፖሊሲዎችን በመንደፍ በርካታ ፕሮጀክቶችን መደገፍ የቻለበትና ውጤት የተመዘገበበት ነበር፡፡ በዚህም በሳይንስና ትምህርትና የዘርፉ ተመራማሪዎች ከፍተኛ ትኩረት እንዲሰጠው መሰረት ተጥሏል፡፡

6. ለሶስተኛ ጊዜ ለውጥ በማካሄድ በአዋጅ ቁጥር 7/1988 የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ በሚል ስያሜ ለውጥ ተካሂዷል፡፡ በመቀጠል በአዋጅ ቀጥር 604/2001 በሚኒስቴር መ/ቤት ደረጃ የተዋቀረ ሲሆን ከሁለት ዓመት በኋላ ደግሞ ተጨማሪ ማሻሻያዎችን በማድረግ ለሀገሪቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ጉልህ አስተዋፅኦ የሚያደርጉ የሳይንስና ቴክኖሎጂ እንቅስቃሴዎችን ማስተባበር፣ ማበረታታትና መደገፍ የሚል ተልዕኮን ይዞ በአዋጅ ቁጥር 691/2002 ዓ.ም አሁን ያለውን ቅርፅ ይዞ በሚኒስትር ደረጃ ሊዋቀር ችሏል፡፡ ሚኒስትር መስሪያ ቤቱም የተሰጠውን ተልዕኮ በላቀ ደረጃ ለማሳካት የተለያዩ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በመቅረፅ ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል፡፡ ከነዚህም ውስጥ የመጀመሪያው የሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚኒስቴር ደረጃ ከተቋቋመ ጀምሮ ቅድሚያ ትኩረት ከሰጣቸው አበይት ተግበራት መካከል የሀገሪቱን የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ እንደገና መቅረፅ ነው፡፡

7. የፖሊሲ ረቂቅ የማዘጋጀቱ ሥራ በ2001 ዓ.ም. ተጀምሮ በተዘጋጀው የፖሊሲ መነሻና ማብራሪያ ሰነድ ላይ ከዓለማቀፍ የፖሊሲ ባለሙያዎችና ከልዩ ልዩ የባለድርሻ አካላት አስተያየቶችንና ግብዓቶችን በመሰብሰብ፣ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ ከመቅረፅና ከመተግበር አንፃር ከፍተኛ ልምድ ያላቸው ዓለም አቀፍ ኤክስፐርቶችና በሀገር ውስጥ ከሚገኙ ዋና ዋና የዘርፍ መ/ቤቶች፣ ከዩኒቨርስቲዎች፣ ከምርምር ተቋማትና ከኢንዱስትሪው ዘርፍ የተውጣጡ ባለሙያዎች የተሳተፉበት ውይይት እንዲሁም በኮሪያ፣ በጀርመንና በኔዘርላንድ ከሚገኙ ዩኒቨርስቲዎች የመጡ ከፍተኛ ኤክስፕርቶች በረቂቁ ላይ ያላቸውን አስተያየትና በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ አፈፃፀም ያላቸውን ተሞክሮና የተገኙ ግብአቶችን በማካተት በተለያዩ ጊዜ

በሚኒስትሮች ምክር ቤትም ተመክሮበትና ግብአቶች በሰፊው ታክሎበት ተጠናቆ የካቲት 21/2004 ዓ.ም በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሀገሪቱ ካቢኔ ተቀባይነት አግኝቶ የፀደቀ ሲሆን ሚኒስትር መ/ቤቱ በድጋሚ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008/ ዓ.ም እንደገና ተወስኗል፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይና ተልዕኮ

### ራዕይ

8. በ2015 ዓ.ም. ሀገራችን ውጤታማ የሆኑ የውጭ ቴክኖሎጂዎችን በፍጥነት የመማር፣ የማላመድ እና የመጠቀም አቅሟ ተገንብቶ ማየት፡፡

### ተልዕኮ

9. ለሀገሪቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ጉልህ አስተዋፅኦ የሚያደርጉ የሳይንስና ቴክኖሎጂ እንቅስቃሴዎችን ማስተባበር፣ ማበረታታትና መደገፍ፡፡

## የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፖሊሲ ዋና ዋና ዓላማዎች

- በጠንካራ ትብብር ላይ የተመሰረተና ለተቀናጀ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን አቅም ግንባታ እንቅስቃሴ አጠቃላይ የሆነ አመራር ማዕቀፍ መፍጠር፣
- ቴክኖሎጂዎችን በአግባቡ ለማሸጋገር ሀገራዊ የቴክኖሎጂ አቅም መፍጠር የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት፣
- ቴክኖሎጂ በመማር እና በማላመድ ላይ ያተኮረ የምርምር አቅም መገንባት፣
- ሀገር በቀል ዕውቀቶችንና ቴክኖሎጂዎችን ማልማትና ጥቅም ላይ ማዋል፣
- ሀገራዊ የሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ምህዳር(Landscape) በግልጽ በማስቀመጥ በኢኖቬሽን ሥርዓቱ ውስጥ ባሉ ተዋናዮች መካከል ያለው ትስስር ማጠናከር፣
- የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን እንቅስቃሴዎች ከሌሎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ፕሮግራሞችና ዕቅዶች ጋር ተቀናጅተው መተግበራቸውን ማረጋገጥ፣
- የግሉ ዘርፍ የቴክኖሎጂ ሽግግር ሥራዎችን በማከናወን እና በመደገፍ ረገድ ያለው ሚና በቀጣይነት እያደገ እንዲሄድ ለማድረግ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠር

የሚሉት ናቸው፡፡

## የሚኒስትር መ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር

10. የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 ዓ.ም መሠረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ተሰቶታል፣

- የሀገሪቱን የልማት አቅጣጫ መሠረት ያደረገ የሣይንስና ቴክኖሎጂ ምርምርና ልማት ኘሮግራም ያዘጋጃል፤ በመንግስት ሲፀድቁም ተግባራዊ እንዲደረገ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፣ ይገመግማል፣
- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የቴክኖሎጂ ፍላጎት ለመዳሰስ፣ ቴክኖሎጂዎችን ለማፈላለግ፣ ለመምረጥ፣ ለማስገባት፣ ለመቀመር፣ ለመጠቀም እና ለማስወገድ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤
- በየዘርፉ በሽግግር የሚመጡ ቴክኖሎጂዎችን መረጃ ይመዘግባል፣ ሞዲፋይ የማድረግና የማቀብ ሥራዎችን ያስተባብራል፣ ለቀጣዩ ሥራ እንቅስቃሴም እንዲውሉ ያደርጋል፤
- የሣይንስና ቴክኖሎጂ ልማት እንቅስቃሴዎችንና ሀገራዊ የምርምር ፕሮግራሞችን ያስተባብራል፤ የሚካሄዱ የምርምር ሥራዎች ከሀገሪቱ የልማት ፍላጎት ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ያረጋጋጣል፤
- የሣይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን መረጃ ቋት ያደራጃል፣ መረጃዎችን ያጠናቅራል፤ አገራዊ የመረጃ አያያዝ ደረጃ ያወጣል፤ የሣይንስና ቴክኖሎጂ ኢኖቬሽን አመላካቾችንም ያዘጋጃል፣ ለአገልግሎት እንዲውሉ ያደርጋል፤
- በመንግሥትና በግል የከፍተኛ ትምህርትና የምርምር ተቋማት እና በኢንዱስትሪው ዘርፍ መካከል ለምርምርና ቴክኖሎጂ ልማት እንቅስቃሴ የሚያግዝ ምቹ የርስበርስ ትስስርና ቅንጅታዊ አሠራር እንዲፈጠር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
- የሀገሪቱን የረዥም ጊዜ የሣይንስ፣ የቴክኖሎጂ፣ የኢኖቬሽንና የጥራት መሠረተ ልማት የሰው ኃይል ልማት ያቅዳል፣ ተግባራዊነቱንም ይከታተላል፤ የሀገሪቱ ሥርዓተ ትምህርት ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ልማት አንፃር መቃኘቱን ለማረጋገጥ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ይተባበራል፤
- በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ በሣይንስና ቴክኖሎጂ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ ተቋማትና ባለሙያዎች አቅም የሚገነባበትን ሁኔታ በማመቻቸት ረገድ ድጋፍ ይሰጣል፤

- ለሣይንስና ቴክኖሎጂ ልማትና ለፈጠራ ሥራዎች እድገት አስተዋጽኦ ላበረከቱ ግለሰቦችና ተቋማት ሽልማትና ማበረታቻ የሚሰጥበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ተግባራዊም ያደርጋል፤
- የምርምር ሥራዎችን ለማስተባበር የሚያግዙ ምክር ቤቶችንም ያቋቁማል፣ ያስተባብራል፣ ይደግፋል፤
- ለሣይንስና ቴክኖሎጂ መዳበር የበለጠ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ የሙያ ማኅበራትንና አካዳሚዎችን ያበረታታል፤ ይደግፋል፤
- የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማትን ለማሳደግ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የቴክኖሎጂ ፍላጐትን ይለያል፤ አግባብነት ያላቸውና ዕሴት የሚጨምሩ የቴክኖሎጂ መረጃዎችን አደራጅቶና ተንትኖ ለተጠቃሚዎች ያቀርባል፤
- የሣይንስና ቴክኖሎጂ ነክ ተቋማትን ይመራል፤ ለአገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ያላቸውን አስተዋጽያ ያረጋግጣል፡፡

## የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር አደረጃጀት እና የሰው ኃይል

### ድርጅታዊ መዋቅር

11. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመራው የተቋሙ የበላይ አመራር በሆኑ በአንድ ሚኒስትር እና በሁለት ሚኒስትር ዴኤታዎች ሲሆን ተጠሪነቱም ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ነው፡፡ በመሆኑም አንድ የሚኒስቴር ፅ/ቤት ዋና ዳይሬክተር፣ ሶስት ዳይሬክተር ጀነራሎች፣ አስር ዳሬክቶሬቶች  እና አስራ ሦስት ደጋፊ የስራ ሂደቶች እንዲኖሩት ተደርጐ ተዋቅሯል፡፡
12. በተጨማሪም በሥሩ አስራ አንድ/የኢትዮጵያ ጨረር መከላከያ ባለስልጣን፣ የኢትዮጵያ አምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት፣ የኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ፣ ብሔራዊ የሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት የመሳሰሉት/ የራሳቸው የሆነ “Autonomous” አደረጃጀት ያላቸው ተጠሪ ተቋማትን ያስተዳድራል፡፡ ድርጅታዊ መዋቅሩ ከዚህ ሪፖርት ጋር **በአባሪ** (2) ተያይዟል፡፡

### የሰው ኃይል

13. ሚኒስቴር መ/ቤቱ 351 የሰው ኃይል እንዲኖሩት በመዋቅር የተፈቀደለት ሲሆን በታህሳስ ወር 2010 ዓ.ም ወንድ 118 እና ሴት 78 በድምሩ 197 ሰራተኞች ሲኖሩት 154 በሰው ኃይል ያልተያዘ/ክፍት/ የስራ መደብ አሉት፡፡ የሰራተኞች ፕሮፋይል በትምህርት ደረጃ ሲታይ ኘሮፌሰር አንድ (1)፣ ፒ.ኤች.ዲ እና ዶክትሬት ሶስት (3)፣

ማስተርስ ዲግሪ አስራ አራት(14)፣ ዲግሪ አንድ መቶ ሃያ(120)፣ ዲፕሎማ ሃያ (20) እና በክፍል ደረጃ ሰላሳ ዘጠኝ(39) በጠቅላላው 197 ሠራተኞች በሚኒስትር መ/ቤቱ ይገኛሉ፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ

14. የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በአዋጅ የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን ከመንግስት በጀት የሚመደብለት ሲሆን ከ2007 እስከ 2009 በጀት ዓመት የተመደበለት በጀትና የወጣው ወጪ በሚከተለው ሰንጠረዥ የተመለከተው ነው፡፡

| በጀት ዓመት | ተፈቀደ በጀት | ስራ ላይ የዋለ በጀት | ሥራ ላይ የዋለው በጀት በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| 2007 | 137,729,048.00 | 131,530,441.00 | (95%) |
| 2008 | 100,540,368.00 | 96,887,563.92 | (96%) |
| 2009 | 260,787,621.00 | 177,592,856.97 | (68%) |

## የኦዲቱ ዓላማ

15. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ ውጤታማ እና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ ማከናወኑን መገምገም ሲሆን፣ በዚህ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦች ማቅረብ ነው፡፡

## የኦዲት አከባቢ (Potential Audit Area)

16. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area) በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም የሚል ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues)

17. ከላይ ለተጠቀሰው የኦዲት አካባቢ ሶስት/3/ የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ እነሱም፡-
    1. ቴክኖሎጂዎችን የማፈላለግ፣ የመምረጥ እና የማስገባት ስራዎችን አፈፃፀም ወጪ ቆጣቢ፣ና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፣
    2. ቴክኖሎጂዎችን የማላመድ፣ የመጠቀም እና የማስወገድ ስራዎችን አፈፃፀም ወጪ ቆጣቢ፣ና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፣

3. በቴክኖሎጂ የተደገፈ መረጃ አያያዝ እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩን መገምገም፣

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

18. ከላይ ለተቀመጡት ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች 34 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶችን ለማዘጋጀት መሠረት የሆኑት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተቋቋመበት አዋጅ፣ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲና የፖሊሲ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂ፣ ከ2007-2009 ዓመታት ያሉት ዕቅድና የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች፣ የአምስት ዓመት ስትራቴጂ ዕቅድ/ከ2008-2012/፣ ዩኒቨርሲቲ ኢንዱስትሪ ትስስር መመሪያ፣ ዓመታዊ መፅሄቶች፣ ብሮሸሮች እና መልካም ተሞክሮዎች ሲሆኑ የተዘጋጁት የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ስራው ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) **በአባሪ 1** ተያይዟል፡፡

## የኦዲቱ ወሰን

19. ኦዲቱ የተከናወነው በአለምአቀፍ የክዋኔ የኦዲት ደረጃዎች (ISSAI) በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ስታንደርድ (Ethiopian Performance Audit Standard) እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ሲሆን ኦዲቱ በዋነኛነት የሚሸፍነው ሶስት የበጀት ዓመታትን ከ2007 እስከ 2009 ያሉትን ሲሆን የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት አፈፃፀም ውጤታማነትን በተመለከተ የተከናወነ ነው፡፡

## የኦዲቱ ዘዴ


20. ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሲሆን የተለያዩ የሰነድ እና በኤሌክትሮኖክስ ቅጅ (soft copy) የቀረቡ መረጃዎች በመከለስ፣ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች፣ የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ፣ አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ፣ በናሙና የተመረጡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፣ ለኦሮሚያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ፣ ለኢትዮጵያ ቆዳ ልማት ኢንስቲትዩት፣ ለኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንስቲትዩት፣ ለኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዮት፣ ለፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ፣ ለአዲስ አበባ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ቢሮ፣ ለአዲስ አበባ ተግባረ

ዕድ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ፣ ለጀነራል ዊንጌት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ እና ለምስራቅ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ/ ቃለ መጠይቅ በማቅረብ እና የመስክ ምልከታ በማድረግ ነው፡፡

Office of the Federal Auditor General

## የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት ትኩረት መስክ ስዕላዊ መግለጫ /System Description/

የትኩረት መስክ፡- የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት ውጤት፡ ! - የተሸጋገረና የለማ ቴክኖሎጂ



## ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

### 2.1. ቴክኖሎጂዎችን የማፈላለግ፣ የመምረጥ እና የማስገባት ስራዎች አፈፃፀም ወጪ ቆጣቢና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፣

**ቴክኖሎጂዎችን ለማፈላለግ፣ ለመምረጥ እና ለማስገባት የሚያስችል አዋጅ፣ ደንብና መመሪያዎች መውጣታቸውንና ተግባራዊ መደረጋቸውን በተመለከተ፣**

21. ሚኒስቴር መ/ቤቱ ቴክኖሎጂዎችን ለማፈላለግ፣ ለመምረጥ እና ለማስገባት እንዲያስችለው አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያዎች ሊያወጣና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

22. በኦዲቱ ወቅት በሀገር አቀፍ ደረጃ ቴክኖሎጂን ለማሸጋገር የሚረዳ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢኖቬሽን ፖሊሲ በ2004 ዓ.ም፣ ፖሊሲውን ማስፈፀሚያ ስትራቴጂ በ2006 ዓ.ም እና የትምህርትና ስልጠና፣ የምርምር ተቋማት እና የኢንዱስትሪ ትስስር የአሰራር መመሪያ 2006 ዓ.ም ተዘጋጅተዋል፡፡ ይሁን እንጂ ቴክኖሎጂን ለማፈላለግ ለመምረጥ፣ ወደ አገር ውስጥ ለማስገባትና ለመጠቀም የሚረዳ ረቂቅ ደንብ በ2005 ዓ.ም በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጀ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልጸደቀ መሆኑ ታውቋል፡፡

23. በተጨማሪም በናሙና ተመርጠው ቃለ መጠይቅ ከቀረበላቸው የአዲስ አበባ ተግባረዕድ፣ ምስራቅ፣ ጀኔራል ዊንጌት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ፣ የአዲስ አበባ ከተማ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ቢሮ እና የፌደራል ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኤጀንሲ የስራ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ቴክኖሎጂን ለማሸጋገር መሟላት ያለበት አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ባለመኖሩ የእውቀት ማነስ፣ የቴክኖሎጂ የመቅዳት ጥራት ጉድለት እንዲሁም የማላመድ ችግሮች እንደገጠማቸው ገልፀዋል፡፡

24. በመሆኑም የሚኒስትሩ የበላይ ኃላፊዎች ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ በሀገር ደረጃ እንዲረጋገጥ የሚታሰበውን የቴክኖሎጂ ሽግግር ውጤታማ በማድረግ ረገድ ያሉበትን ክፍተቶች መሠረት በማድረግ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተለያዩ ሀገራትን ልምድ መሠረት በማድረግ ከጥቂት ዓመታት በፊት ቴክኖሎጂን ለማፈላለግ፣ ለመምረጥ፣ ለማስገባት፣ ለማላመድና ለማስወገድ የሚያስችል ወጥ አዋጅ ለመቅረፅ ሰፊ እንቅስቃሴ አድርጓል በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

25. ቴክኖሎጂዎችን ለማፈላለግ፣ ለመምረጥ እና ለማስገባት የሚያግዙ ደንብ እና መመሪያዎች ባለመኖራቸው ለአገሪቱ ጠቃሚ የሆኑትም ሆነ ያልሆኑት ቴክኖሎጂዎች ወጥነት በሌለበት በተዘበራረቀ ሁኔታ ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ ወይም ኮፒ እንዲደረጉ ለማድረግ በር ከመክፈቱም ባሻገር ወደሀገር ውስጥ የገቡ ቴክኖሎጂዎች እንዳይታወቁና በሚፈለገው ደረጃ ቴክኖሎጂዎች እንዳይሸጋገሩ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**ቴክኖሎጂን ለማሸጋገር ለሚሰሩ የምርምር ፕሮግራሞችን ድጋፍ መደረጉን በተመለከተ፣**

26. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቴክኖሎጂ ሽግግርን በተመለከተ ልማታዊ እንቅስቃሴዎችንና ሀገራዊ የምርምር ፕሮግራሞችን ሊያስተባብር እና የገንዘብ እና ሌሎችን የተለያዩ ድጋፎችን ሊያደርግ ይገባል፡፡

27. በሚኒስቴር መ/ቤቱ ችግር ፈቺ ተብለውና ተለይተው ለሚወጡ የምርምር ስራዎች ተወዳድረው ላለፉ ተወዳዳሪዎች የሚደረግ የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋል፡፡ ይሁን እንጂ ተመራማሪዎቹ ለምርምር ስራው አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች በሚደረገው የገንዘብ ድጋፍም መግዛት/ማሟላት/ የማይቻል መሆኑ፣ በአዲስ አበባና በአዳማ ለሚገኙ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲዎች ለምርምር ስራ የሚያመቹ ግብዓቶች /ያሉት ላብራቶሪዎች/ ያልተሟሉ መሆኑ፤ ይህም የምርምር ስራውን ከማሳካት አንፃር እንቅፋት እየፈጠረባቸው መሆኑን በናሙና ተመርጠው ቃለ መጠይቅ የቀረበላቸው የአዲስ አበባና አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲዎች፣ የአዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት እና የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

28. በተጨማሪ በኦዲቱ በናሙና የታዩ የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ፣ የአዲስ አበባ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ቢሮ፣ የምስራቅና የጀኔራል ዊንጌት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች ቴክኖሎጂዎችን ከማፈላለግም ሆነ ኮፒ ከማድረግ አኳያ በሚደረግ እንቅስቃሴ ምንም ዓይነት ድጋፍ ያልተደረገላቸው መሆኑን፣ ቴክኖሎጂዎችን በራሳቸው ጥረት ብቻ የሚቀዱ/ኮፒ/ የሚያደርጉ በመሆኑ ቴክኖሎጂዎችን የመቅዳት አቅም ውስንነት የፈጠረና በዩኒቨርስቲዎች መካከል ያለው ግንኙነት የላላ እንዲሆን ያደረገ መሆኑ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ ከሰጡት ምላሽ ለመረዳት ተችሏል፡፡ በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ፣ ለኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዮት፣ ለቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ለምርምር ስራ አሸንፈው ከሚደረገው የገንዘብ ድጋፍ በተጨማሪ የትስስር መመሪያና የተለያዩ

ማንዋሎችን ከመላክ ውጪ ቴክኖሎጂ ሽግግርን በተመለከተ የተደረገ ድጋፍ የሌለና ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

29. ስለ ጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የቴክኖሎጂ ሽግግር ዳይሬክተር ጄነራል ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር የሚመራ የሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ምክር ቤት ተቋቁሟል፡፡ ስራውንም ወደ መሬት ለማውረድ ብሄራዊ የምርምር ካውንስል፣ ብሄራዊ የትምህርት ስልጠና የምርምርና ኢንዱስትሪ ትስስር አደረጃጀቶች ያሉ ሲሆን በቴክኖሎጂ ሽግግርና በተቋማት መካከል ያለውን ትስስር ለማሳለጥ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴርን ጨምሮ ውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር የተካተተበት በኢኮኖሚና ቢዝነስ ዲፕሎማሲ አገራዊ የቅንጅት መድረክ የቴክኖሎጂ ሽግግር ድጋፍ ኮሚቴ አለ፡፡ ስለዚህ ቴክኖሎጂን በራሳችን እየመረጥን ነው የሚሉ ተቋማት ምንአልባትም የተሟላ መረጃ የሌላቸው በመሆኑ አሊያም በድጋፍ ከሚሰጠው አገልግሎት ይልቅ የራሳቸውን አቅጣጫ በመምረጣቸው ካልሆነ በቀር ያሉበት ውስንነቶች እንደተጠበቀ ሆኖ አሰራሩ ግን በሀገር ደረጃ መዘርጋቱን በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

30. የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማትን በተመለከተ በተለያዩ ተቋማት ሊከናወኑ የሚችሉ ተግባራትን የማስተባበር ኃላፊነት ያለው ሲሆን ይህንንም በተለያየ መንገድ እየፈፀመ ይገኛል፡፡ ከነዚህም ዋና ዋናዎቹ የምርምርና ፈጠራ ስራዎችን በጉልህ እንዲወጡ በተለያዩ ዘዴዎች የማስተዋወቅ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም ለቴክኖሎጂ ምርምርና ፈጠራ ስራዎች ዕውቅና ለመስጠት አዳዲስ ቴክኖሎጂ ያላቸውን ግለሰቦች መርጠው እንዲልኩ የጠቀሱትን ተቋማት በማሳተፍ ዕውቅና የመስጠትና ወደ ስራ እንዲገቡ የፋይናንስና የስልጠና ድጋፎችን የማድረግ ስራ እየሰራ ይገኛል፡፡ ይህንን ተግባር በተሳካ ሁኔታ ለመፈፀም እንዲቻል ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የአደረጃጀት ለውጥ በማድረግ ራሱን የቻለ የስራ ሂደት አቋቁሞ እየሰራ ይገኛል፡፡

31. በተጨማሪ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአዲስ አበባና በአዳማ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲዎች በምርምርና በቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ የተመሰረተን የማስተርስና የፒ.ኤች.ዲ ዲግሪዎችን ሊያሰጡ የሚችሉ ፕሮግራሞች ያሏቸውና ዓለምአቀፍ ደረጃቸውን የጠበቁ 16 የምርምርና የቴኖሎጂ ሽግግር የልዕቀት ማዕከላት በስራቸው በልዩ ሁኔታ እንዲደራጁ ተደርጓል፡፡ እነዚህ የልዕቀት ማዕከላት በሰው ሃይልና በመሳሪያ ሙሉ በሙሉ እስኪደራጁ ድረስ በተጨባጭ የሚፈለገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል በመጠንና በጥራት ለማዘጋጀትና ለምርምር ሥራ የሚያስፈልጉ

ላብራቶሪዎችንና ማቴሪያሎች በማሟላት ላይ ነው ያሉት በመሆኑም የምርምር ላብራቶሪዎች እና ግብዓቶች ከሚጠይቁት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪና ከሚጠይት የግንባታ አንፃር እጥረቶች መኖራቸው የሚጠበቅ ቢሆንም በተጠቀሰው ደረጃ ክፍተት ያለባቸው ተደርገው ሊወሰድ አይገባም፡፡ በሌላም በኩል የሚደረገው የምርምር ድጋፍ በተቻለ መጠን የውጭ ምንዛሪ ወጪን ሳይጠይቁ በሀገር ውስጥ ግብዓት እንዲከናወኑ ነው የሚያበረታታው፡፡ ይህም ሆኖ ምርምሩ በትክክልም ችግር ፈቺነቱ ከታመነበትና ለውጤታማነቱም በውጭ ምንዛሪ የሚገዙ ግብዓቶችን መጠቀም የሚኖርበት ከሆነ ግብዓቱ እንዲቀርብ አስፈላጊውን የማመቻቸት ድጋፍ እንሰጣለን በማለት ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

32. ይሁንና ኃላፊዎቹ ይህን ቢሉም ኦዲቱ በተከናወነበት ጊዜና መጠይቅ በቀረበበት ወቅት በየራሳቸው ቴክኖሎጂ የሚመርጡ ተቋማት ከዚህ ወጥተው ወጥነት ያለው አሰራር እንዲኖር ለማድረግ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትልና ድጋፍ ያላደረገ በመሆኑ ለምርምር የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ባለመሟላታቸው የምርምር ስራዎችን ለማከናወን አስቸጋሪ ያደረገው መሆኑንና ከቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት ጋር በተያያዘ ተገቢው ድጋፍ ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ያማከለ ባለመሆኑ እና በሀገር አቀፍ ደረጃ የተዘረጋው የቴክኖሎጂ ሽግግር ሥርዓት ታች ያለው ፈጻሚ አካላት ድረስ መሬት ወርዶ እንዴት እየተተገበረ መሆኑን ማረጋገጥ የነበረበት በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ እንዳለ መቀበል ያስቸግራል፡፡

33. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቴክኖሎጂ ሽግግር ልማታዊ እንቅስቃሴዎችንና ሀገራዊ የምርምር ፕሮግራሞችን በተገቢው መንገድ የማያስተባብር፣ የሚያስፈልጉት ግብዓቶች የማይሟሉና ከገንዘብ የዘለለ ቴክኒካል እገዛዎችና የሰው ሃይል ማብቃት ላይ ድጋፍ ካልተደረገ የሚጀመሩ ምርምሮች ሊቋረጡና ውጤታማ የሆኑ የምርምር ውጤቶች እንዳይወጡ ሊያደርጋቸው እንደሚችልና ቴክኖሎጂዎች ከሞያ ተቋማት ጀምሮ በሚፈለገው መጠን እንዳይሸጋገሩ ሊያደርግ ይችላል፡፡

### የሀገሪቱን የቴክኖሎጂ ፍላጎትና ክፍተት መሰረት ያደረገና ሊሸጋገሩ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን በጥናት ላይ ተመስርቶ ያፈላለገ መሆኑን በተመለከተ፣

34. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሀገሪቱን የቴክኖሎጂ ፍላጎትና ክፍተት መሰረት ያደረገና ሊሸጋገሩ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን በጥናት ላይ ተመስርቶ ሊያፈላልግና ፍኖተ ካርታ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ የተዘጋጁትን አገራዊ የቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ ፍኖተ ካርታዎች

ለባለድርሻ አካላት በማስተላለፍ ተግባራዊ ሊደረግ እና ተግባራዊነቱን ሊከታተል ይገባል፡፡

35. በኦዲቱ ወቅት መረጃዎችን በመከለስ እና በናሙና ለተመረጡ የስራ ኃላፊዎች ቃለ መጠይቅ በማቅረብ ለማወቅ እንደተቻለው በ20 የተለያዩ ዘርፎች ላይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በጥናት ላይ ተመስርቶ የቴክኖሎጂ ፍኖተ ካርታ ሰነዶች አዘጋጅቷል፡፡ የተዘጋጁትን ፍኖተ ካርታዎች ለኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽን፣ ለኢፌዲሪ ውሀ የመስኖና የኤሌክትሪክ ሚኒስቴር፣ ለቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፣ ለኢፌዲሪ አካባቢ፣ ደንና የአየር ለውጥ ሚኒስቴር፣ ለኢፌዲሪ እርሻና ተፈጥሮ ሐብት ሚኒስቴር፣ ለኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዮትና ለኢትዮጵያ ስኳር ኮርፖሬሽን በመስከረም 2010 ዓ.ም የተላከ መሆኑ ታውቋል፡፡

36. ነገር ግን በኦዲቱ በናሙና በታዩት ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ቢሮ፣ ለፌደራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲ፣ ለአዲስ አበባ ተግባረ ዕድ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ፣ ለምስራቅ እና ለጀኔራል ዊንጌት ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኮሌጆች ፍኖተ ካርታ በሚያዘጋጅበት ወቅት እንዲሳተፉ ያልተደረገና የተዘጋጁትም ፍኖተ ካርታዎች ያልደረሷቸው መሆኑን፣ የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ፣ የአዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት እና አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በሚዘጋጅበት ወቅት ተሳታፊ ቢሆኑም የተዘጋጀው ፍኖተ-ካርታ/ሀርድ ኮፒ/ ያልደረሳቸው መሆኑ ነገር ግን አዳማ ዩኒቨርስቲ በዝግጅቱ ወቅት የተሳተፉበት ሶፍት ኮፒ ያለ መሆኑ ከቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

37. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በአሁኑ ወቅት የተዘጋጁት 20 የፍኖተ ካርታ ሰነዶች በኮሚቴ ደረጃ የተዘጋጁ በመሆናቸው ይዘቱ ወጥነት እንዲኖረው እና በሀገር ደረጃ ሳይንሳዊ ፁሁፎችን በቋንቋ ረገድ ያሉባቸውን ግድፈቶች አስተካክሎ ወደስራ ለማስገባት የአርትኦት ስራ እንዲከናወንና የሽፋን ገፅ ዲዛይን እንዲዘጋጅና እንዲታተም በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ስራውን ወደ ተግባር ለማስገባት ህትመቱ የተጠናቀቀላቸውን የፍኖተ ካርታ ሰነዶች በሃርድ ኮፒ፣ ህትመታቸው በሂደት ላይ ያሉ የፍኖተ ካርታ ሰነዶችን ደግሞ በሶፍት ኮፒ ወደ ሚመለከታቸው ተቋማት የማሰራጨት ስራ መጀመሩን ለቀረበላቸው መጠይቅና ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

38. በተጨማሪ በመውጫ ስብሰባ ወቅት በፍኖተ ካርታ ተሳታፊ ለሆኑት በኤሌክትሮኒክስ ፎርማት የተሰራጨላቸው መሆኑና ለተወሰኑት ባለድርሻ አካላትም በሀርድ ኮፒ የተላለፈ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

39. በሀገር ደረጃ የተዘጋጁትን ፍኖተ ካርታዎች ተጠናቀው በማውጣት ለባለድርሻ አካላት እንዲደርሳቸው በማድረግ ወደ ተግባር እንዲሸጋገሩ ባለመደረጉ የተቀመጡት የቴክኖሎጂ አቅጣጫዎች በወቅቱ እንዳይተገበሩ አድርጓል፡፡

## በየዘርፉ የሚሸጋገሩ ቴክኖሎጂዎችን አመራረጥን በተመለከተ፣

40. የሚኒስቴር መ/ቤቱ በየዘርፉ ሊሸጋገሩ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን ለመምረጥ የሚያስችል ግልጽ የሆነ የመምረጫ መስፈርት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሊያዘጋጅ፣ በመምረጫው መስፈርት መሰረት ቴክኖሎጂዎችን የሚመርጥ ኮሚቴ ሊያቋቁምና መረጣውን ሊያካሂድ ይገባል፡፡

41. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት፡-

- ቴክኖሎጂን ለመምረጥ የሚያስችል የመምረጫ መስፈርት በማዘጋጀት ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣
- በየዘርፉ የሚሸጋገሩ ቴክኖሎጂዎችን በመምረጫው መስፈርት መሰረት የሚመርጥና የሚገመግም በሚኒስቴር መ/ቤቱ በበላይነት የሚመራ ኮሚቴ መቋቋም ሲገባው ያልተቋቋመ መሆኑ፣
- በየዘርፉ ወይም በየተቋሙ ቴክኖሎጂዎች ያለ መምረጫ መስፈርት እየተመረጡ መሆናቸው፣
- ወደ ሀገር ውስጥ በተለያዩ ዘርፎችና ዩኒቨርስቲዎች ቴክኖሎጂዎች በተለያዩ መንገዶች ወጥነት በጎደለው መልኩ ወደ ሃገር ውስጥ የሚገቡና ኮፒ የሚደረጉ መሆናቸውን፣

በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎችና በናሙና ተመርጠው ቃለ መጠይቅ ከቀረበላቸው የአዲስ አበባና የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲዎች፣ የኢትዮጵያ ቆዳ ልማት ኢንስቲትዩት፣ የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብአቶች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፣ የኢትዩጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣ የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ ኃላፊዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

42. ስለ ጉዳዩ የቴክኖሎጂ ሽግግር ዳይሬክተር ጄነራል ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ቴክኖሎጂ መምረጫ መስፈርት በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የተዘጋጀው

ከቴክኖሎጂ ፍኖተ ካርታ ሠነድ ዝግጅቶች ጋር ተጣምሮ የተሰራ ተግባር ነው፡፡ ከዚያ በፊት በነበረው አሰራር ቴክኖሎጂ የመምረጫ መስፈርቶች የቴክኖሎጂ አስገቢ ባለቤቱ ፍላጎትና አቅም ላይ መሠረት ያደረገ ሲሆን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ደግሞ ከሰውና ከአካባቢ ጤንነትና ደህንነት ጋር በተያያዘ በህግ አስገዳጅ ደረጃ የተቀመጠባቸው ቴክኖሎጂዎች እንዳይገቡ የመከላከልና የማገድ አሰራርን ተግባራዊ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጂን መሰረት በማድረግ የካርቦን ልቀታቸው አካባቢን የማይጎዳ ቴክኖሎጂዎች ተመራጭ የሚሆኑበት አሰራር መከተሉ ይህን አመላካች የሚያደርገው ሲሆን በሚኒስትር መ/ቤታችን በሀገር ደረጃ የሚገቡ ቴክኖሎጂዎች የሚመርጥና የሚገመግም ኮሚቴ አልተቋቋመም ምክንያቱም የቴክኖሎጂ ፍኖተ ካርታ ሰነዶች ከመዘጋጀታቸው በፊት በሀገር ደረጃ የተዘጋጀ መስፈሪያ አልነበረም በማለት ገልፀዋል፡፡

43. በተጨማሪ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሀገር ደረጃ የቴክኖሎጂ ሽግግር አቅጣጫን በተመለከተ በመንግስት ዋና ዋና የፖሊሲና ስትራቴጂ ሰነዶች ማለትም ከሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ በተጨማሪ በኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ፣ የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲ፣ ወዘተ ባሉ ሰነዶች ሀገራዊ የልማት አቅጣጫዎች የተቀመጡ መሆኑን፣ የቅድሚያ ትኩረት ዘርፎች ተዘርዝረው የተቀመጡ ከመሆኑ በላይ ሽግግሩን በማሳለጥ ረገድ እንደየዘርፉ ልዩ ባህሪይ አደረጃጀትና አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑ፣ በተጨማሪ በሀገራችን የተነደፈውን የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድን ለማሳካት የሚያግዝ በአገር አቀፍ ደረጃ የኢኮኖሚ እና ቢዝነስ ዲፕሎማሲ የቅንጅት መድረክ መቋቋሙ እና በዚሁ ሀገራዊ የቅንጅት መድረክ ሥር ከተቋቋሙት ኮሚቴዎች መካከል የመሠረተ-ልማትና ኢንጂነሪንግ ዘርፍ ኮሚቴ ይህን አበይት ተግባር በወጤታማነት ለመከወን የተፈጠረ አደረጃጀትና አሰራር መኖሩንና ከዚህ ባሻገር ቴክኖሎጂን የሚመርጠው በኮሚቴ ሳይሆን የሚከናወነው በማምረቻ እና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ውስጥ ሲሆን ይህን ተግባር ደግሞ እንዲደግፉ የቴክኖሎጂ ልማት ኢንስቲትዮቶች ተቋቁመዋል በማለት ገልፀዋል፡፡

44. ኃላፊዎቹ ይህን ምላሽ ይስጡ እንጂ በአገሪቱ ውስጥ የሚደረገውን የቴክኖሎጂ ሽግግር ከተቀመጠው ፖሊሲና ስትራቴጂ አንጻር እየተቃኘ መሆኑን ማረጋገጥና ሂደቱን በበላይነት ማስተባባር ያለበት በመሆኑ እንዲሁም ፍኖተ ካርታው አጠቃላይ አቅጣጫ

ማሳያ እንጂ ዝርዝር የመመርጫ መስፈርት ባለመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

45. በመሆኑም በየዘርፉ ሊሸጋገሩ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን ለመምረጥ የሚያስችል የመምረጫ መስፈርት በማዘጋጀት እና ቴክኖሎጂዎችን በአግባቡ የሚመርጥ ኮሚቴ በማቋቋም ተግባራዊ ካልተደረገ በተለያየ መንገድ የሚገቡ ቴክኖሎጂዎች ለሃገሪቱ ያላቸው ጥቅምና ጉዳት ሳይረጋገጥ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ በማድረግ ከጥቅማቸው ይልቅ የሚያደርሱት ጉዳት እንዲያመዝን እና የተበታተነ የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲኖር ወደ አገር ውስጥ የገቡ የቴክኖሎጂዎች ብዛት እና አይነቶች እንዳይታወቅ ያደርጋል፡፡

**በቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት ዙሪያ የሚከሰቱ ክፍተቶች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የሚገመገሙ መሆኑን በተመለከተ፣**

46. በቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት ዙሪያ በየዘርፉ የሚከሰቱ ክፍተቶች ላይ በዕቅድ በመያዝና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ሊገመገሙ ይገባል፡፡

47. በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩት የአዲስ አበባና የአዳማ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲዎች ተጠሪነታቸው ለሚኒስቴሩ በመሆኑ በሚያቀርቧቸው ሪፖርቶች ላይ ችግሮችን የሚያቀርቡ መሆኑ፣ ነገር ግን በቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት ዙሪያ በሚነሱ ክፍተቶች ላይ ውይይት በማድረግ ያልተገመገሙ ሲሆን በምርምር ስራ ባጋጠመ የውሎ አበል ችግር ላይ ችግሩ የሚፈታበትን ሁኔታ በመስከረም 2010 በደብዳቤ መልስ መስጠቱን ገልጸዋል፡፡ ይሁን እንጂ በቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት ዙሪያ በየዘርፉ የሚከሰቱ ክፍተቶችን በመለየትና በዕቅድ በመያዝ ከተገልጋዮችና ከባለድርሻ አካላት ጋር የውይይት መድረክ በማዘጋጀት የማይገመገሙ መሆኑን በናሙና በታዩት የፌደራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኤጀንሲ፣ የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣ የአዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፣ የአዲስ አበባ ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ቢሮ፣ የአዲስ አበባ ተግባረዕድ፣ የምስራቅ እና የጄኔራል ዊንጌት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የስራ ኃላፊዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ከሰጡት ምላሽና በኦዲቱ ወቅት ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

48. ስለ ጉዳዩ የቴክኖሎጅ ሽግግር ዳይሬክተር ጀነራል ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በቴክኖሎጂ ሽግግር ዙሪያ የሚነሱ ችግሮችን መሠረት በማድረግ ውይይቶች በየጊዜው

ይካሄዳሉ፡፡ ሆኖም ግን ሁሉንም ባለድርሻ አካላት በሚፈለገው ደረጃ ከማሳተፍ አንፃር ብሎም ከአለው ድርጅታዊ አቅም አንጻር ክፍተቶች እንዳሉ ገልፀዋል፡፡

49. በተጨማሪ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚያከናውናቸው ሁሉም ሀገራዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ እንቅስቃሴዎች ሁሉ ከተገልጋይና ባለድርሻ አካላት ጋር በዕቅድ የግንኙነት ጊዜ ፈጥሮ የሚገመግም መሆኑ፣ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት በተውጣጡ የተደራጀው ብሄራዊ የምርምር ካውንስልና የትምህርት፣ ሥልጠና የምርምር ተቋማትና ኢንዱስትሪ ትስስር ፎረም በተጨማሪ በስሩ ካደራጃቸው የሕዝብ ክንፍ አካላት ጋር በጋራ አቅዶ በጋራ አፈፃፀምን እንደሚገመግም፣ በሌላም በኩል በቴክኖሎጂ ሽግግር እና ልማት ዙሪያ በየዘርፉ የሚከሰቱ ክፍተቶችን ለመቅረፍ ይረዳ ዘንድ በመንግስት የልማት ትኩረት አቅጣጫን በመከተል በተለዩ 9 ዘርፎች በየዓመቱ ዕቅድ በማዘጋጀት፣ በችግሮች ላይ የዳሰሳ ጥናት በማካሔድ እና በጥናቱ መሰረት ለተለዩ ችግሮች የመፍትሔ እርምጃዎች ወስዷል፡፡ ነገር ግን ከተቋሙ አሰራር ጋር በተያያዘ ያሉትን ውስንነቶች ከማሳየት አንፃር ችግሮችን ሙሉ በሙሉ መፍታት የሚያስችል የሰለጠነ የሰው ኃይል እና የበጀት ውስንነት እንዳለ ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል በማለት ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

50. በመሆኑም በቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት ዙሪያ በየዘርፉ የሚከሰቱ ክፍተቶችን ከባለድርሻ አካላት በተለይም ለሽግግሩ አይነተኛ መሳሪያ ከሆኑት የምርምር፣ የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ጋር ችግሮቹን ለመቅረፍ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዕቅድ በመያዝና ግምገማ አለማካሄዱ በቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ የራሱን የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡

## 2.2 ቴክኖሎጂዎችን የማላመድ፣ የመጠቀም እና የማስወገድ ስራዎችን አፈፃፀም ወጪ ቆጣቢና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ

### ቴክኖሎጂዎችን ለማፈላለግ፣ ለማላመድና ለመጠቀም የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ መሰጠቱን በተመለከተ፣

51. ቴክኖሎጂዎችን ለማፈላለግ፣ ለማላመድና ለመጠቀም የሚያስችል ወጥ የሆነና በዕቅድ የተያዘ የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሀ ግብር በማውጣት ለሚመለከታቸው አካላት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

52. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ እንደተቻለው ስለ ሚኒስቴር መ/ቤቱ አጠቃላይ ግንዛቤ የሚሰጥ ቢሆንም በቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት፤ ከማፈላለግ፣ ከማላመድ፣

ከመጠቀምና ከማስወገድ አንፃር በተለየ መልኩ ግንዛቤ ማስጨበጥን በተመለከተ በናሙና ተመረጠው ከታዩትም ውስጥ፡-

- የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት የምርምር ፅሁፎች እንዴት መዘጋጀት እንዳለበትና የዩኒቨርስቲ ኢንዱስትሪ ትስስርን በተመለከተ የተሰጡ ግንዛቤዎች መኖራቸው፣
- የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በ2008 ዓ.ም በሚ/ር መ/ቤቱ በተዘጋጀ ወርክ ሾፕ ላይ ተሳታፊ እንደነበሩና በ2009 ዓ.ም ከሲሚንቶ ፋብሪካ ጋር በመተባበር በሚኒስቴር መ/ቤቱ በተዘጋጀ የጋራ መድረክ እንዲሳተፉ የተደረገ ቢሆንም የቴክኖሎጂ ሽግግርን አስመልክቶ የግንዛቤ ማስጨበጫ ያልተሰጠ መሆኑ፣
- የአዲስ አበባ ተግባረዕድ እና ምስራቅ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጂ በ2007 ዓ.ም አንድ ጊዜ ብቻ እንዲሳተፉና በ2008 እና 2009 ዓ.ም እንዲሳተፉ የተደረገበት አግባብ የሌለ መሆኑ፣
- የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በ2009 ዓ.ም. ለዩኒቨርስቲ ተመራማሪዎች በተዘጋጀ የምርምር ፕሮጀክት ፕሮፖዛል አዘገጃጀት ትንተና ላይ አንድ ባለሙያ እንዲሳተፍ ከማድረግ ውጭ ሌላ ከቴክኖሎጂ ሽግግር ጋር በተያያዘ የተሳተፉበት አግባብ የሌለ መሆኑ፣
- የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ፣ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ቢሮ፣ የጀኔራል ዊንጌት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ፣ የኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣ የኦሮሚያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ፣ የአዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት እና የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ የቴክኖሎጂ ሽግግርን በተመለከተ የውይይት መድረኮች ላይ እንዲሳተፉ ያልተደረገና ግንዛቤ ማስጨበጫ ያልተሰጠ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት በተደረገ ቃለ መጠይቅ ከሰጡት ምላሽ ለማወቅ ተችሏል፡፡

53. ስለጉዳዩ የሚኒስቴሩ ኃላፊዎች ተጠይቀው ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከቴክኖሎጂ ሽግግር ጋር በተያያዘ በራሱ በሚኒስቴሩና በስሩም ባሉ ተጠሪዎች አማካኝነት ቴክኖሎጂዎችን ለማፈላለግ፣ ለማለማመድና ለመጠቀም ወጥ የሆነና በእቅድ የተያዙ በርካታ የግንዛቤ መስጫ ፕሮግራሞች የተከናወኑ መሆኑን ነገር ግን በተለያየ ደረጃና አግባብ እስከታች መውረድ እንደሚኖርበት እንደሚያምኑ ገልጸዋል፡፡ ከዚህም መነሻ በቀጣይ የሃያ አራት ሰዓታት የቴሌቪዥን ስርጭት የተጠናከረ ግንዛቤ ፈጠራ ተግባራትን ለማከናወን በእንቅስቃሴ ላይ ሲሆን እንደ ግብርና ኤክስቴሽን ሀገራዊ ድጋፍ ሁሉ

በቴክኖሎጂ ሽግግር ላይም ተመሳሳይ የግንዛቤና የቴክኒክ ድጋፍ መሠጠት የሚችልበትን የኢንዱስትሪ ቴክኖሎጂ ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አስፈላጊነትን በመፈተሽ ላይ እንገኛለን በማለት ገልፀዋል፡፡

54. ይሁንና ኃላፊዎቹ ቴክኖሎጂዎች ለማፈላለግ፣ ለማላመድና ለመጠቀም በዕቅድ የተያዙ በርካታ የግንዛቤ መስጫ ኘሮግራሞች ተከናውነዋል ይበሉ እንጂ ግንዛቤ የተሰጡበት ምንም ዓይነት መረጃ ያልቀረበ በመሆኑ ተሰጥቷል የተባለውን የግንዛቤ ማጨበጫ ተግባራትን ለማረጋገጥ ያዳግታል፡፡

55. በመሆኑም የቴክኖሎጂ ሽግግር ለሚመለከታቸው አመንጪ፣ አስተላላፊ እና ፈጻሚ ለሆኑ ባለድርሻ አካላት ወጥ የሆነና በዕቅድ የተያዘ የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሃ ግብር በማውጣት ተግባራዊ አለመደረጉ ሊሸጋገሩ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎች እንዳይሸጋገሩና ቴክኖሎጂዎችን ከማፈላለግ አኳያ የዕውቀት ማነስና በቂ ግንዛቤ እንዳይኖራቸው ከማድረጉም ባሻገር ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ጋር በቅርብ እንዳይሰሩ ያደርጋቸዋል፡፡

## ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ቴክኖሎጂዎች በተለያዩ የማስታወቂያ ዘዴዎች ለህብረተሰቡ የሚተዋወቁ ስለመሆኑ፣

56. ከተለያዩ ሀገራት ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ተደራሽና ተደማጭ በሆኑ በማስታወቂያ ዘዴዎች በመጠቀም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ለተጠቃሚው እና ለህብረተሰቡ ሊያስተዋውቅ ይገባል፡፡

57. ይሁን እንጂ ሚኒስቴር መ/ቤቱ፡-

- በየአመቱ በሚያሳትመው ልሳነ ሳይንስ መጽሄት ላይ በሀገር ውስጥ ኮፒ የተደረጉ የፈጠራ ስራዎችን እና የተወሰኑ ቴክኖሎጂዎችን የሚያስተዋውቅ ቢሆንም በቂ አለመሆኑ፣
- ለሚኒስቴር መ/ቤት ተጠሪ የሆነው የመረጃ ማዕከል በሚያዘጋጀው የሳምንት የ30 ደቂቃ የቴክ ሳይንስ የቴሌቭዥን ፕሮግራምና የቴክ ሳይንስ መፅሔት ላይ የተወሰኑ ቴክኖሎጂዎችን የማስተዋወቅ ስራ ቢሰራም ለሁሉም የህብረተሰብ አካላትና ተቋማት ተደራሽ አለመሆኑ፣
- አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ተደራሽና ተደማጭ በሆኑ የማስታወቂያ ዘዴዎችን በመጠቀም የማያስተዋውቅ በመሆኑ ተጠቃሚ አለመሆናቸውን፣

በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ቃለ መጠይቅ ከቀረበላቸው ባለድርሻ አካላት እና ከተከለሱ የሰነድ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

58. ስለ ጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ከማስተዋወቅ አኳያ ሚኒስቴር መ/ቤታችን በሚያሳትመው ልሳነ ሳይንስና በሚያካሂዳቸው ወርክሾፖች የሚያስተዋወቅና ግንዛቤ የሚፈጥር ሲሆን በስሩ ያለው የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከል ቴክ ሳይንስ መፅሄትና በሳምንት አንዴ የሚተላለፈውን የቴሌቪዥን ፕሮግራም በመጠቀም ግንዛቤ ይፈጥራል፡፡ ሌሎች ተጠሪ ተቋማትም በተለይም ደግሞ የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በዚህ ዘርፍ ሰፌ እንቅስቃሴ ከሚያደርጉ ተቋማት መካከል ግንባር ቀደም ነው፡፡ ይህም ሆኖ ከሚፈለገው የግንዛቤ ፈጠራ ጋር ሲነፃፀር አጠቃላዩ እንቅስቃሴ ክፍተት ያለበት በመሆኑ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የ24 ሠዓት የቀጥታ የቴሌቪዥን ሥርጭት ለመጀመር በእንቅስቃሴ ላይ ይገኛል በማለት ገልፀዋል፡፡

59. በተጨማሪም በሀገር ደረጃ የቴክኖሎጂ ሽግግርን ውጤታማነት ከማረጋገጥ አኳያ ሀገራዊ የሳይንስ ባህል ግንባታ አስፈላጊ እንደሆነ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ስለሚያምን አደረጃጀት ፈጥሮ በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በማፀደቅ የሳይንስ ባህል ግንባታ ዳይሬክቶሬትን ያቋቋመ ሲሆን ዝግጅቱ እንደተጠናቀቀም ወደስራ የሚገባበት ይሆናል፡፡ በተለያዩ የህትመት፣ የኤሌክትሮኒክና ሳይበር ሚዲያዎችን በመጠቀም አዳዲስና ችግር ፈቺ የምርምር ውጤቶችን በስፋት ለማስተዋወቅ ጥረቶች እየተደረገ ነው በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

60. በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በተጠሪ ተቋሙ የሚታተሙ መፅሔቶች ለህብረተሰቡ ተደራሽ ከመሆን አንፃር በቂ ባለመሆናቸውና ወደሀገር ውስጥ አዳዲስ ሆነውም ሆነ በሀገር ውስጥ ኮፒ የተደረጉ ቴክኖሎጂዎችን ተደራሽና ተደማጭ በሆኑ የማስታወቂያ ዘዴዎችን በመጠቀም ባለማስተዋወቁ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች በቀላሉ ለተቋማትም ሆነ ለማህበረሰቡ ተደራሽ ሆነው ጥቅም ላይ እንዳይውሉ ያደርጋቸዋል፡፡

### አገልግሎት የማይሰጡ ቴክኖሎጂዎች የሚወገዱበት ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፣

61. ሚኒስቴር መ/ቤቱ አዳዲስ ሆነው አገልግሎት የማይሰጡም ሆኑ አገልግሎት ሰጥተው ተበላሽተው የተቀመጡ ቴክኖሎጂዎችና ተጓዳኝ ዕቃዎች በባለሙያ ተረጋግጠውና

ተለይተው በአግባቡ ሊወገዱ የሚችልበት ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

62. ይሁን እንጂ የጨረር አገልግሎት ሰጥተው የተበላሹ እቃዎችን በኢትዮጵያ ጨረር መከላከያ እንዲወገዱ የሚደረግበት ሁኔታ ከመኖሩ ውጭ በናሙና ተመርጠው በታዩ ዩኒቨርሲቲዎች፣ በመካከለኛና ከፍተኛ ማምረቻና አገልግሎት መስጫ ተቋማት እና በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ተቋማት ውስጥ የሚገኙ አገልግሎት የማይሰጡ ቴክኖሎጂዎችና ተጓዳኝ ዕቃዎች በሚኒስቴር መ/ቤቱ የማይታወቁ መሆኑ፣ በባለሙያ ተረጋግጠውና ተለይተው የሚወገዱበት ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

63. ስለ ጉዳዩ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በተጨባጭ መሬት ላይ ካለው ሁኔታ መረዳት እንደሚቻለው ሁሉም ወደሀገራችን የገቡ ቴክኖሎጂዎችና ተጓዳኝ ዕቃዎች የአገልግሎት ዘመናቸውን ከጨረሱ በኋላ በሠውና አካባቢ ላይ ጉዳት በማያደርሱበት አግባብ እየተወገዱ ነው ማለት አይቻልም፡፡ ግን ደግሞ ተቋማት የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት መሠረት በማድረግ የማስወገድ ስራ በማከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡ እንደአብነት ለመጥቀስም ከኮምፒዩተር ጋር የተያያዙ መሳሪያዎችን በአሁኑ ሠዓት በሠውና በአካባቢ ላይ ጉዳት እንዳያደርሱ የማስወገዱን ተግባር የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ሚኒስቴር እያከናወነ ሲገኝ የኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ ደግሞ ከጨረራ አመንጪ መሳሪያዎች ጋር የተያያዙ መሳሪያዎችን የማስወገድ ተግባር በማከናወን ላይ ይገኛል፡ ለዚሁ ተግባር የሚረዳ ትልቅ ማጠራቀሚያ ወደአስር ሚሊዮን ብር በሚጠጋ የመንግስት በጀት ማከማቻ አዘጋጅቷል፡፡ የአገልግሎት ጊዜያቸውን የጨረሱ የጨረራ አመንጪዎችን በዚሁ ማከማቻ ማእከሉ ውስጥ ነው በጊዜያዊነት እያከማቸ የሚገኘው፡፡ ይሁን እንጂ በሰውና በአካባቢ በአሁኑና በመጪው ትውልድ ጭምር ጉዳት የሚያስከትሉ ቴክኖሎጂዎች እነዚህ ብቻ ባለመሆናቸው እግር በግር ተከትሎ በዘላቂነት ማስወገድ ያስፈልጋል፡፡ ቅንጅታዊ አሰራርም መኖር ይኖርበታል በማለት ገልጸዋል፡፡

64. የኮምፒውተርና የጨረር አገልግሎት የሰጡ ዕቃዎች ላይ የማስወገድ ጅምር ስራ ቢኖርም በአጠቃላይ አዳዲስ ሆነው አገልግሎት የማይሰጡም ሆኑ አገልግሎት ሰጥተው ተበላሽተው የተቀመጡ ቴክኖሎጂዎች የሚወገዱበት ስርዓት አለመዘርጋቱ በተለያዩ ተቋማት/ዘርፎች/፣ ዩኒቨርስቲዎችና በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ላይ ያለአገልግሎት የተቀመጡ ቴክኖሎጂዎችና ተጓዳኝ ዕቃዎች

እንዳይታወቁ፣ ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉም እንዳይለዩና አገልግሎት የማይሰጡትንም ቴክኖሎጂዎች በሰውና በአካባቢ ላይ ጉዳት በማያደርሱበት መንገድ በባለሙያ ተለይተው በወቅቱ አለመወገዳቸው በሰውና በእንስሳት እንዲሁም በአካባቢ ላይ የሚያደርሱት ጉዳት ከፍተኛ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

## የቴክኖሎጂዎችን በአግባቡ ለማሸጋገር ሀገራዊ የቴክኖሎጂ አቅም መፍጠር የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፣

65. ቴክኖሎጂዎችን በአግባቡ ለማሸጋገር ሀገራዊ የቴክኖሎጂ አቅም በመፍጠር የሚያስችል ስርዓት በሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

66. ቴክኖሎጂን በማሸጋገር ሀገራዊ የቴክኖሎጂ አቅም ለመፍጠር እንዲቻል ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ2006 ዓ.ም የትምህርትና ስልጠና፣ የምርምር ተቋማት እና የኢንዱስትሪ ትስስር የአሰራር መመሪያ አዘጋጅቷል፡፡ ነገር ግን እስካሁን ድረስ 17 የቀጠና ፎረም አስተባባሪዎች ከመመስረትና በትስስሩ የሚሳተፉ ባለድርሻ አካላት ትውውቅ ከመከናወኑ ባለፈ በትስስሩ የተከናወኑ ተግባራት ላይ ውስንነት መኖሩና ለውጥ ያመጣ ስራ ያልተሰራ መሆኑ፣ ከቴክኒክና ሙያ ትምህርት ተቋማትም ሆነ ከዩኒቨርስቲዎች የሚወጡ ተማሪዎች የተማሩትን ትምህርት በተግባር ለመፈፀም ወደ ተለያዩ የኢንዱስትሪ ተቋማት በሚላኩ ጊዜ ተቋማቱ በተማሩት ትምህርት ላይ የማይመደቡ በመሆናቸው ትክክለኛውን ዕውቀት ይዘው የማይወጡ መሆኑን በናሙና ተመርጠው ቃለ መጠይቅ ከቀረበላቸው ባለድርሻ አካላት ለማወቅ ተችሏል፡፡

67. ስለጉዳዩ የቴክኖሎጂ ሽግግር ዳይሬክተር ጄነራል በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ የትምህርት ሚኒስቴርና የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታዎች የሚመራ ብሔራዊ የትምህርት ስልጠናና የምርምርና የኢንዱስትሪ ትስስር አደረጃጀትና አሰራር ፈጥሮ በሀገር ደረጃ 17 ቀጠናዊ 84 ንዑስ ቀጠናዊ ትስስሮች ተፈጥረው እየተሰሩ ይገኛል፡፡ በዚህ ትስስር ዋነኛ ዓላማ የንድፈ ሀሳብ እውቀትና የተግባር ልምምድ በምርምርና ልማት ተደግፎ በኢንዱስትሪ ውስጥ አቅም እንዲገነባ ሀገራዊ የቴክኖሎጂ አቅም ለመገንባት የሚደረጉ ጥረቶች መጀመራቸውን ትስስሩ በየጊዜው እየተሸሻለ እየሄደ ቢሆንም የአደረጃጀትና የአሰራር ችግሮች አሉበት፡፡ ለምሳሌ፡-

- አንድ ተማሪ ልምምድ ወጥቶ አንዱ ኢንዱስትሪ ቢሄድና አደጋ ቢደርስበት ወይም በማሽን ላይ ጉዳት ቢያደርስ ኃላፊነቱን ሊወስድ የሚገባው አካል

አልተለየም፡፡ ስለዚህ ኢንዱስትሪዎች ተማሪን ለመቀበል ሙሉ በሙሉ ፈቃደኛ አይደሉም፡፡

- እንደ ኢንዱስትሪዎቹ ሁሉ የዩንቨርሲቲ ተመራማሪዎችም የኢንዱስትሪውን ችግር የሚፈታ ምርምር ለማከናወን የሚመደብ በጀት ባለመኖሩ ትስስራቸው ጥብቅና ውጤታማ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡

በመሆኑም ማዕቀፉ በትክክል ችግር የሚፈታበትና የንድፈ ሃሳብም የተግባርም እውቀትና ክህሎት የሚቀሰምበት አሰራርና አደረጃጀት እንዲሆን ክፍተቶቹን ነቅሶ በማውጣት ማሻሻያዎችን ማካሄድ ያስፈልጋል በማለት አብራርተዋል፡፡

68. በተጨማሪ የትምህርት ስልጠና የምርምር ተቋማት እና የኢንዱስትሪ ትስስር መመሪያ እና የዚህ አደረጃጀት ተግባራዊ እንቅስቃሴ በዋናነት ዩኒቨርሲቲ እና ምርምር ተቋማት የኢንዱስትሪውን ችግር የሚፈቱ ምርምሮች፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር ተግባራት፣ የአቅም ግንባታ ስራዎች በጋራ የሚከናወኑበት ብቻ ሳይሆን ዩኒቨርሲቲው የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋሙንና የኢንዱስትሪውን የሰው ኃይል አቅም ክፍተት እንዲሞላ እንዲሁም የዩኒቨርስቲ እና የቴክኒክና ሙያ ሰልጣኞች ተግባራዊ ዕውቀት በኢንዱስትሪው እንዲቀስሙ ለማስቻል ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የውጤታማነት ደረጃው ውስንነቶች ያሉት ቢሆንም እንደሀገር ቴክኖሎጂያዊ እድገት ደረጃ ጅምር ስራዎች ያሉ መሆናቸውን ገልጸው የተገኙ ተጨባጭ ውጤቶች እንዳሉም በሜድሮክ ኩባንያ፣ በዩኒቲ ዩንቨርስቲና በማዕድን ልማት ዘርፍ የተከናወኑትን አመርቂ ውጤቶች ማሳያ አድርጎ መውሰድ ይቻላል በማለት ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

69. በተጨማሪ በመውጫ ስብሰባ ወቅት የተገኙ ኃላፊዎች የኢንዱስትሪ ትስስርን በተመለከተ ከትውውቅ ያለፈ ስራ በዚህ ዓመት እየተሰራ ያለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

70. ቴክኖሎጂዎችን በአግባቡ ለማሸጋገር ሀገራዊ የቴክኖሎጂ አቅም መፍጠር ዋነኛ ወሳኝ ጉዳይ በመሆኑና የዩኒቨርስቲ ኢንዱስትሪ ትስስሩ በተጠናከረ ሁኔታ ካልተሰራበት የአሰልጣኞች የእውቀት ማነስ፣ የውጭ ቴክኖሎጂዎችን የመቅዳት አቅም ውስንነት፣ የፈጠራ ስራዎች መዳከም፣ የዕውቀት ሽግግር ማነስ እና በቴክኒክና ሙያ ስልጠና ተቋማትና ዩኒቨርሲቲ መካከል ያለው ግንኙነት የላላ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

**ችግር ፈቺ ተብለው የሚከናወኑ ምርምሮች ወደ ተግባር የሚሸጋገሩ መሆኑን በተመለከተ፣**

71. በከፍተኛ ምርምር ተቋማት የሚከናወኑ ምርምሮችና ጥናቶች ወደ ተግባር የሚሸጋገሩበትን ሥርዓት ሚ/ር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

72. ይሁን እንጂ ለሀገሪቱ ከፍተኛ ጥቅም ያላቸው በከፍተኛ ምርምር ተቋማት የሚሰሩ ምርምሮች እና ጥናቶች ተለይተው ወደ ተግባር ሊሸጋገሩ የሚችሉበት ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለናሙና ከታዩትም ውስጥ፡

- ለአዲስ አበባ ተግባረዕድ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በ2008 ዓ.ም አንድ ልጅ በሰራው ምርምር እንዲሸለም ከማድረግ ውጭ ወደ ተግባር እንዲሸጋገር የተደረገበት አግባብ የሌለ መሆኑ፣
- ለፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኤጀንሲ፣ የአዲስ አበባ ቴክኒክና ሙያ ስልጠና ቢሮ፣ የምስራቅ ጀኔራል ዊንጌት ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ፣ የኦሮሚያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ፣ የአዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፣ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት፣ የአዳማ እና የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲን ሚ/ቴር መ/ቤቱ የፈጠራ ስራን ከመሸለምና ምርምሮችን አወዳድሮ የገንዘብ ድጋፍ ከማድረጉ ውጪ ወደ ተግባር እንዲለወጡ ያልተደረገ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በምርምር የተደረሰባቸው፣ የፈለቁ ወይም የተቀዱ ቴክኖሎጂዎች ወደ ምርትና ምርታማነት አለመቀየራቸው፣
- የቴክኖሎጂ ማበልፀጊያ ማዕከላት ያልተቋቋሙ መሆናቸው፣

73. ስለጉዳዩ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ሥርዓት ተዘርግቷል ትስስሩ ጠንካራና ውጤታማ አይደለም ክፍተቶች አሉበት፡፡ በያዝነውም በጀት ዓመት ይህንኑ ክፍተት በመለየት የተጠናከረ አሰራርን ለመፍጠር ተገቢ እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ እና በእነዚህ ትስስሮች የሚከናወኑ ምርምሮች ወደምርትና አገልግሎት መሸጋገር እንዲችሉም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ድጋፍ በማድረግ ላይ ነው፡፡ ባለፈው በጀት ዓመት ለፋይናንስ ድጋፍ ከቀረቡ የትስስር ምርምር ፕሮጀክቶች መካከል 7 ለሚሆኑት ችግር ፈቺ ምርምሮች ማካሄጃ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ድጋፍ አድርጓል፡፡ ትልቁ ችግር እና ቁልፍ ጉዳይ በትስስሩ ማአቀፍ ውስጥ የሚካሄዱ

አብዛኞቹ የምርምር ፕሮጀክቶች ወደምርትና አገልግሎት የማይሸጋገሩት በራሳቸው በምርምሮቹ ድክመት እና በተያያዝ ባሉ ድጋፎች እጥረት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

74. በተጨማሪም በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመራ የኢኖቬሽን ምክር ቤት መቋቋሙ በስሩም የሳይንስና ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ምክር ቤት ተቋቁሞ በአጭር ጊዜ ወደ ምርት ሊቀየሩ የሚችሉ የምርምር ስራዎች የሚደገፋበት የአሰራር መመሪያ ከሀገሪቱ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኢኖቬሽን ፖሊሲ አንፃር በመቃኘት የተዘጋጀና በኢኖቬሽን ምክር ቤት ከሀገሪቱ የዕድገትና የልማት ፍላጎት ጋር የሚሄዱ ቅድሚያ የተሰጣቸው የምርምር ርዕሶችን ቅደም ተከተል በማውጣት ከጸደቀ በኋላ ከ2007 በጀት ዓመት ጀምሮ ከ32 በላይ ለሚሆኑ ችግር ፈቺ የምርምር ስራዎች ለእያዳንዳቸው ከ5 ሚሊዮን ብር የፋይናስ ድጋፍ በማድረግ እየሰራ ይገኛል በማለት ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

75. በመሆኑም በከፍተኛ ምርምር ተቋማት መምህራን እና ተማሪዎች ከፍተኛ ወጪ ወጥቶባቸው የሚሰሩ ምርምሮችና ጥናቶች ወደ ተግባር የሚሸጋገሩበትን ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ካልተደረገ የወጣው ወጪ ችግር ሳይፈታ እንዲሁ እንዲባክን፣ ጥናቶች በመደርደሪያ/ሸልፍ ላይ ከመቀመጥ እንዳይዘሉ እና የተጠኑ የምርምር ስራዎች ተግባራዊ እንዳይሆኑ ያደርጋል፡፡

## 2.3. በቴክኖሎጂ የተደገፈ መረጃ አያያዝ እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩን በተመለከተ

### የቴክኖሎጂ መረጃ አያያዝ እና ሥርጭትን ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፣

76. በሚኒስቴር መ/ቤቱ በመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች፣ በከፍተኛ ትምህርት እና በምርምር ተቋማት መካከል ጠንካራ የቴክኖሎጂ ሽግግር መረጃ አያያዝ ስርዓት ሊዘረጋና መረጃዎቹንም ሊሰበስብ፣ ሊተነትንና በተደራጀ መልክ ሊይዝ ይገባል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት ዙሪያ የተተነተኑትና የተደራጁ መረጃዎችን በዘመናዊ መንገድ ለሚመለከታቸው አካላት ሊያስተላለፍ ይገባል፡፡

77. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች፣ ከከፍተኛ ትምህርት እና ከምርምር ተቋማት ጋር በዘመናዊ መንገድ የተደገፈና የተደራጀ የቴክኖሎጂ መረጃ አያያዝና ልውውጥ ማድረጊያ ስርዓት ያልዘረጋ መሆኑ፣ በየዘርፉ በሽግግር ወደሀገር ውስጥ የገቡም ሆኑ በሀገር ውስጥ ኮፒ የተደረጉ

ቴክኖሎጂዎች ተመዝግበው ያልተያዙና የማይታወቁ መሆኑ፣ በቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት ዙሪያ አግባብነት ያላቸውና ዕሴት የሚጨምሩ የቴክኖሎጂ መረጃዎችን ተንትኖ ለተጠቃሚዎች ያላደረሳቸው መሆኑን ከተከለሱ መረጃዎችና ቃለ መጠይቅ ከቀረበላቸው ኃላፊዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

78. ስለጉዳዩ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ብሎም በከፍተኛ ትምህርትና ምርምር ተቋማት መካከል የሚካሄዱ ቴክኖሎጂ ሽግግር መረጃዎችን ከመመዝገብ አንፃር የመረጃ ክፍተት ምንጭ የሆነው በሀገር ደረጃ የቴክኖሎጂ ሽግግር የሕግ ማዕቀፍ ባለመኖሩ የተነሳ ምዝገባ ሥርዓቱን ደካማ አድርጎታል፡፡ ከዚያ አልፎ ያሉት መረጃዎችን መዝግቦ ከማስተላለፍ አንፃርም በሰራተኞች መልቀቅ እንዲሁም የወረቀት መረጃዎች ሙሉ በሙሉ ወደዲጂታል ከመሸጋገሩ በፊት የቢሮ ለውጥ በመደረጉ ሀገራዊ ሁኔታዎችን የሚያመለክቱ መረጃዎች ክፍተት እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ መረጃን በመያዝ የቴክኖሎጂዎችን መረጃ የሚይዘው የሳይንስና ቴክኖሎጂ የመረጃ ማዕከል ሲሆን፣ የደረጃዎች ደረጃ ደግሞ ከሁለቱ ባማያንስ መልኩ የሚያዘው፡፡ የመረጃ ማዕከልም የውጪ ቴክኖሎጂዎችን ነው የሚይዘው በሀገር ደረጃ በጣም በትንሹ እሱም አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ደግሞ ከፓተንት ሰነዶች ጋር በተያየዘ የሚሰራው፣ የአእምሯዊ ንብረት የፈጠራ ስራ ተብለው የሚያዙት ነገር ግን የተዘረጋ ስርዓት የለም ቴክኖሎጂዎች ገና ሲገቡ አስገዳጅ ነገር ባለመኖሩና ከተለያዩ አካላት ጋር መናበብ ባለመኖሩ ነው በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

79. የቴክኖሎጂ ሽግግር የሚካሔደው በማኒፋክቸሪንግ እና በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት መካከል ሲሆን ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በነዚህ ተቋማት መካከል የሚካሔደው ቴክኖሎጂ ሽግግር ለማፋጠን የሚረዱ የህግ ማዕቀፎችን በመፍጠር እና ሌሎች ቴክኒካል ድጋፍ በማድረግ ስራዎችን በማከናወን የሚፈለገው የኢኮኖሚ ዕድገት በተቀመጠለት ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መሰረት እንዲመዘገብ ማድረግ ሲሆን የሚኒስቴር መ/ቤቱ ተጠሪ ተቋም የሳይንስ ቴክኖሎጂ የመረጃ ማዕከል ውስጥ እዲደራጅ ይደረጋል፡፡ የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት ጀነራል ዳይሬክቶሬት በማኒፋክቸሪንግ እና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ያሉባቸውን ችግሮች በጥናት በመለየት የቴክኖሎጂ መረጃን ከአእምሯዊ ልማት ጽ/ቤት ጋር በመተባበር የፓተንት መረጃዎች ላይ እሴት በማከል እንዲሁም ከተለያዩ ምንጮች/ድህረ-ገጾች/ በማፈላለግ

የቴክኖሎጂ መረጃዎችን ለተለያዩ ተቋማት በየዓመቱ ሲያሰራጭ ቆይቷል በማለት ለነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጡት ምላሽ ላይ ገልፀዋል፡፡

80. ኃላፊዎቹ የሳይንስና ቴክኖሎጂ የመረጃ ማዕከል የቴክኖሎጂ ሽግግርን መረጃ የሚይዘው ቢሉም ወደሀገር ውስጥ የገቡ ቴክኖሎጂዎችንም ሆነ በሀገር ውስጥ ኮፒ የተደረጉትን መረጃዎች ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ የተያዘ መረጃ የሌለ መሆኑን ነገር ግን ማዕከሉ በአሁኑ ጊዜ መረጃዎችን በመጠይቅ ለመሰብሰብ እየሰራ እንዳለና የማዕከሉ ዌብ ሳይት ላይም ዲጂታል ላይብረሪ በሚል የተለያዩ ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን መፅሀፎች በመጫን ባለድርሻ አካላት እንዲጠቀሙ የሚደረግበት ሁኔታ ተጀምሮ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት ዲጂታል ላይብረሪውን በአዲስ መልክ እየተሰራና በቅርብ ቀን አገልግሎቱ የሚቀጥል መሆኑን ካነጋገርናቸው የማዕከሉ ኃላፊ ተገንዝበናል፡፡

81. በመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች፣ በከፍተኛ ትምህርት እና በምርምር ተቋማት ውስጥ ያሉ የምርምር ሥራዎች፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት መረጃዎች በአግባቡ ተደራጅተውና በየመልኩ ተለይተው እንዲቀመጡ ባለመደረጉ እስካሁን ምን ያህል ቴክኖሎጂዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንደገቡ እንይታወቅ፣ የገቡት ሁሉ አገልግሎት ላይ መዋል አለመዋላቸው እንዳይታወቅ ከማድረጉ ባለፈ ለወደፊት ለሚሰሩ ስራዎች ግብዓት እንዳይሆኑ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪ በቴክኖሎጂ ሽግግር ዙሪያ ያሉ መረጃዎች ተጠናክረው ለተጠቃሚው ባለመድረሱ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች በፍጥነት ወደሀገር እንዳይገቡ ወይም ኮፒ እንዳይደረጉ ሊያደርግ እንደሚችል ሊታወቅ ይገባል፡፡

**የቴክኖሎጂ ፍላጎትን ለመዳሰስ፣ ለማፈላለግ፣ ለመምረጥ፣ ለማስገባት፣ ለመቀመር፣ ለመጠቀምና ለማስወገድ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፣**

82. የአገሪቱን የቴክኖሎጂ ፍላጎትን ለመዳሰስ፣ ለማፈላለግ፣ ለመምረጥ፣ ለማስገባት፣ ለመቀመር፣ ለመጠቀምና ለማስወገድ የሚያስችል ስርዓት ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ሊዘረጋ፣ ተግባራዊ ሊደረግና አፈፃፀሙን ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

83. ይሁን እንጂ መ/ቤቱ የቴክኖሎጂ ፍላጎትን ለመዳሰስ፣ ለማፈላለግ፣ ለመምረጥ፣ ለማስገባት፣ ለመቀመር፣ ለመጠቀምና ለማስወገድ የሚያስችል ስርዓት ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በመዘርጋት ተግባራዊ ያላደረገ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

84. ስለሁኔታው የቴክኖሎጂ ሽግግር ዳይሬክቶሬት ጄነራል ተጠይቀው ስርዓቱ ተዘርግቷል ነገር ግን በተቋማት መካከል የተጠናከረ መናበብና ቅንጅት ባለመኖሩ የተነሳ የተዘረጋው ስርዓት ተጠናክሮ ወጥነት ባለውና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ የመተግበርን ደረጃ ዝቅተኛ አድርጎታል በማለት ገልፀዋል፡፡

85. በመቀጠል የበላይ ኃላፊዎች በነባራዊ ሁኔታ ላይ የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት አዋጅ ተጠናቆ ወደስራ ባለመግባቱ ወጥ የአሰራር ስርዓት የተዘረጋ ባይሆንም ይህንን ተግባር ማከናወን የሚያስችል ተቋማዊ አሰራር አለ በማለት ገልፀዋል፡፡

86. የአገሪቱን የቴክኖሎጂ ፍላጎትን ለመዳሰስ፣ ለማፈላለግ፣ ለመምረጥ፣ ለማስገባት፣ ለመቀመር፣ ለመጠቀምና ለማስወገድ የሚያስችል ስርዓት ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ባለመዘርጋቱ ወደ ሀገር ውስጥ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ወጥነት ባለው መልኩ እንዳይገቡ፣ ጐጂ የሆኑ ቴክኖሎጂዎች እንዲገቡና ውጤታማ ቴክኖሎጂዎችን በማስገባት የውጭ ምንዛሪ አለአግባብ እንዲባክን ሊያደርግ ይችላል፡፡

**አገር በቀል የቴክኖሎጂ መረጃዎች በሚኒስቴር መ/ቤቱ ድረ-ገፅ ላይ መቀመጣቸውን በተመለከተ፣**

87. አገር በቀል አዳዲስ የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት መረጃዎችና የምርምር ውጤቶችን በማሰባሰብ በሚ/ር መ/ቤቱ ድረገፅ ላይ ሊቀመጡ ይገባል፡፡

88. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ የተቻለው ሀገር በቀል አዳዲስ የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት መረጃዎችና የምርምር ውጤቶች የተቋሙን አቅም እና የቴክኖሎጂ ፍላጎት መሰረት በማድረግ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ድረ-ገፅ ላይ ያልተቀመጡ በመሆኑ ማስተላለፍ ያለበትን መረጃዎች እያስተላለፈ እንዳልሆነና ተጠቃሚዎች የሚፈልጉትን መረጃ እንዳያገኙ እያደረገ መሆኑን በናሙና ተመርጠው ቃለ መጠይቅ ከቀረበላቸው አካላትና ድረ-ገጹን በመመልከት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

89. ለሚኒስቴሩ የበላይ ኃላፊዎች ስለሁኔታው ተጠይቀው የሀገር በቀል ቴክኖሎጂ እና ዕውቀት ልማት ስራ ሂደት ከተቋቋመ አጭር ጊዜ ቢሆንም ለቴክኖሎጂ ሽግግርና ለምርምር ስራ ድጋፍ የሚረዱ አዳዲስ ሀገር በቀል ቴክኖሎጂችና ምርምር ውጤቶችን በማመልከት በሀገር በቀል ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት አማካኝነት የማሰባሰብና ተደራሽ የማድረግ ስራ ለማከናወን በ2010 በጀት ዓመት ዕቅድ መሰረት በመጀመሪያው ሩብ ዓመት ከዝግጅት ምዕራፍ ጋር በሚጣጣም መልኩ በቅድሚያ የቴክኖሎጂ እና የምርምር ውጤቶቹን ለማሰባሰብ የሚያስችል ዝግጅት የተከናወነ

ሲሆን ከዚሁ ጎን ለጎን መረጃዎቹን በማሰባሰብ ሂደት ለማፋጠን ይረዳ ዘንድ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን ጋር ውይይት ተደርጎ በተወሰኑ አካባቢዎች መረጃዎቹን የማሰባሰብ ስራ በ2ኛው ሩብ ዓመት ተጀምሯል፡፡ መረጃ የማሰባሰብ ሂደቱ ገና በሂደት ላይ ያለና የተጠናቀቀ ባለመሆኑ ለተጠቃሚዎች በሚኒስቴር መ/ቤቱ ድረ ገጽ ላይ ተደራሽ ለማድረግ አልተቻለም በማለት ገልፀዋል፡፡

90. በመሆኑም የተቋማቶችን አቅም መሰረት ያደረጉ ሀገር በቀል አዳዲስ የቴክኖሎጂ ሽግግር መረጃዎችና የምርምር ውጤቶችን በሚኒስቴር መ/ቤቱ ድረ-ገፅ ላይ እንዲቀመጡ ባለመደረጉ መረጃዎች በተገቢው መንገድ ለባለድርሻ አካላት ተደራሽ እንዳይሆኑ ከማድረጉ በተጨማሪ የቴክኖሎጂን መረጃ የሚፈልጉ አካላት ለተጨማሪ እንግልትና የጊዜ ብክነት እንዲጋለጡ ያደርጋል፡፡

## የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት አገልግሎት የሚሠጡ ተቋማት በክልሎች መቋቋማቸውን በተመለከተ፣

91. በክልሎች የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን በማቋቋም ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጡ ክትትልና ድጋፍ ሊደረግ ይገባል፡፡

92. በኦዲቱ ወቅት የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ቢሮ፣ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሳይንስና ቴክኖሎጂና ኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ኮሚሽን እና የጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ ቢሮዎች ከተከፈቱ ከ2 ዓመት በላይ በመሆናቸው ስራ በደንብ የጀመሩ መሆኑ፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሳይንስና ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ ጥር/2009 ዓ.ም፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ልማት ኤጀንሲ ከተቋቋመ ገና ሰባት ወሩ ግንቦት 2009 ዓ.ም ሲሆን የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ልማት ኤጀንሲ ደግሞ ሐምሌ 2008 ዓ.ም የተከፈቱ ሲሆኑ በቀሪዎቹ ማለትም በሐረሪ፣ በሱማሌና በአፋር ክልሎችና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ቢሮዎች ያልተቋቋሙ/ያልተከፈቱ/ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

93. በስጉዳዩ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በትግራይ፣ በአማራና በጋምቤላ ክልሎች ቢሮው ከተከፈቱ 2 ዓመት አካባቢ እና ከዛ በላይ በመሆኑ ስራም በደንብ እየተሰራ ይገኛል ነገር ግን በአዲስ አበባ፣ በኦሮሚያና በደቡብ ክልል ከተከፈቱ ዓመትና ከዛ በላይ/ጀማሪ/ በመሆናቸው ስራዎች በተጠናከረ ሁኔታ ወደፊት ይሰራሉ

በሌሎቹም/በሐረሪ፣ አፋርና ሱማሌ ክልሎችና በድሬደዋ ከተማ አስተዳደር/ ላይ የሳይንስና ቴክኖሎጂ አደረጃጀት እንዲፈጠሩ በክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች የካቢኔ አባላት ማለትም ርዕሰ መስተዳድሮችና ከንቲባዎችን ጨምሮ በተገኙበት የሳይንስና ቴክኖሎጂ አደረጃጀት አስፈላጊነት ሰነድ ቀርቦ ውይይት በማድረግ የማሳመን ስራ ተሰርቷል፡፡ እንዲሁም እንደ መነሻ ሊያገለግል የሚችል ሰነድ እና መነሻ አዋጅ ተዘጋጅቶ እንዲደርሳቸው ተደርጓል በማለት ገልፀዋል፡፡

94. በመሆኑም በሁሉም ክልሎች እና ከተማ መስተዳድሮች ላይ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ቢሮዎች /ኤጀንሲዎች/ እንዲቋቋሙ ባለመደረጉ በክልሎች ላይ የሚደረጉ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራዎች የተዳከመ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

## ክፍል ሶስት

## መደምደሚያ

95. በሚኒስቴር መ/ቤቱ የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማትን ለማፋጠን የሚከናወኑ የስራ ተግባራት አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑ ሲገመገም የሚከተሉት ዋና ዋና ግድፈቶች ተገኝተዋል፡፡

- ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ቴክኖሎጂን ለማፈላለግ ለመምረጥ፣ ለማስገባት፣ ለመጠቀምና ለማስወገድ የተዘጋጀ ረቂቅ ደንብ አዲቱ እስከተጠናቀቀ ድረስ ያልጸደቀ መሆኑ፣
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ ችግር ፈቺ ተብለው ለተለዩ ምርምሮች ማከናወኛ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግ ቢሆንም ለምርምር ስራ የሚስፈልጉ ሌሎች ግባዕቶችና ላብራቶሪዎች ያልተሟሉ መሆኑ፣
- የሀገሪቱን የቴክኖሎጂ ፍላጎትና ክፍተት መሰረት ያደረጉ በ20 የተለያዩ ዘርፎች ላይ በሚ/ር መ/ቤቱ የቴክኖሎጁ ፍኖተ ካርታ ሰነዶች የተዘጋጁ ቢሆንም ታትመው ለሚመለከታቸው ዘርፎችና ተጠቃሚዎች ያልተሰራጩ መሆኑን፣
- ወደአገሪቱ ሚገቡትን የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን ለመምረጥ የሚያስችል የመምረጫ መስፈርት ያልተዘጋጀ መሆኑ፣
- በቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት ዙሪያ የሚከሰቱ ክፍተቶች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ሚኒስቴር መ/ቤቱ የማይገመገም መሆኑ፣
- ቴክኖሎጂዎችን ለማፈላለግ፣ ለማላመድና ለመጠቀም የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ ተግባራት ለባለድርሻ አካላት ያልተሰጠ መሆኑ፣
- ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ሆነ በአገር ውስጥ የሚፈጠሩ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለህብረተሰቡ ለማስተዋወቅ የሚሰራው ሥራ አነስተኛ መሆኑ፣
- አዳዲስ ሆነው በተለያየ ምክንያት አገልግሎት የማይሰጡ ሆኑ አገልግሎት ሰጥተው ተበላሽተው የተቀመጡ ቴክኖሎጂዎች የሚወገዱበት ሥርዓት ያልተዘረጋ እና ምን ያህል መወገድ ያለባቸው ቴክኖሎጂዎች እንዳሉ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የማይታወቁ መሆኑ፣
- ቴክኖሎጂዎችን በአግባቡ ለማሸጋገር ሀገራዊ የቴክኖሎጂ አቅም መፍጠር የሚያስችል የትምህርት ስልጠና፣ የምርምር ተቋማት እና የኢንዱስትሪ ትስስር ለመፍጠር ስርዓት የተዘረጋ ቢሆንም ትስስሩ የአሰራር ችግር ያለበት መሆኑ፣

- ችግር ፈቺ ተብለው ለሚከናወኑ ምርምሮች በሚኒስቴር መ/ቤቱ  በሚደረግ የገንዘብ ድጋፍ የተከናወኑ ምርምሮች ወደ ተግባር የሚሸጋገሩበት ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፣
- በምርምር የተደረሰባቸውና ወይም የተቀዱ ቴክኖሎጂዎች ወደ ምርትና ምርታማነት ያልተቀየሩ መሆኑ፣
- የቴክኖሎጂ ማበልፀጊያ ማዕከላት አለመቋቋማቸው፣
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት መረጃዎችን ለመያዝ በቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ አያያዝ ስርዓት የዘረጋ ቢሆንም ወደ ሀገር ውስጥ የገቡና ኮፒ የተደረጉ ቴክኖሎጂዎች ተመዝግበው ያልተያዙና የማይታወቁ መሆኑ፣
- ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የቴክኖሎጂ ፍላጎትን ለመዳሰስ፣ ለማፈላለግ፣ ለመምረጥ፣ ለማስገባት፣ ለመቀመር፣ ለመጠቀምና ለማስወገድ የሚያስችል ስርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፣
- አገር በቀል የቴክኖሎጂ መረጃዎች በሚኒስቴር መ/ቤቱ ድረ-ገፅ ላይ እንዲቀመጡና ለህዝብ እንዲደርሱ ያልተደረገ መሆኑ፣
- የሳይንስና ቴክኖሎጂን የሚመለከቱ አደረጃጀቶች የሌላቸው ክልሎች መኖራቸው፣

96. ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት  የተገኙትን  ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

# የማሻሻያ ሀሳቦች

97. የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ ቅንጅታዊ የአሰራር ስርዓት በመፍጠር የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማትን አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ስኬታማ ሆነው ጥራት ያለው እና ተጠቃሚውን የሚያረካ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማስቻል እንዲሁም በተለያዩ ዘርፎች ላይ በቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት ዙሪያ ላይ ተመሳሳይ ክፍተቶች እንዳይከሰቱ ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን የማሻሻያ ሀሳቦች አቅርበናል፡-

- በቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት ዙሪያ የሚያገለግል በረቂቅ ደረጃ የሚገኘው ቴክኖሎጂን ለማፈላለግ፣ ለመምረጥ፣ ለማስገባት፣ ለመጠቀም፣ ለማላመድና ለማስወገድ በ2005 ዓ.ም. የተዘጋጀው ደንብ የወቅቱን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ተከልሶ እና በባለድርሻ አካላት ተገምግሞ በአስቸኳይ በሚመለከተው አካል ጸድቆ ተግባራዊ በማድረግ ወደ ትግበራ ሊሸጋገር ይገባል፡፡ በተጨማሪ ደንቡን ለማስፈፀም የሚረዱ መመሪያዎች ሊዘጋጁና ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ ችግር ፈቺ ተብለው ለተለዩ ምርምሮች ከሚደረገው የገንዘብ ድጋፍ በተጨማሪ ምርምሩን ለማሳካት የሚያግዙ ግባዕቶች በተለይም ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ተጠሪ በሆኑት በአዲስ አበባና በአዳማ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲዎች የላብራቶሪ ማዕከላት የሚሟላበት መንገድ በማቻቸት በቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት ምርምር ዙሪያ የሚሰጠውን ድጋፍ ሊያሳድግ ይገባል፡፡
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሀገሪቱን የቴክኖሎጂ ፍላጎትና ክፍተት መሰረት ባደረጉ የተለያዩ 20 ዘርፎች ላይ የተዘጋጁት የፍኖተ ካርታ ሰነዶች በሙሉ የአርትኦት ሥራቸው እና ህትመታቸውን በማጠናቀቅ እና ለሚመለከታቸው አካላት በማሰራጨት ወደ ተግባር እንዲገቡ ሊደርግ እና አፈጻጸሙም ላይ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡
- በሀገር ውስጥ የሚገቡ ቴክኖሎጂዎችን ለመምረጥ የሚያስችል ለየዘርፉ የሚያገለግል የመምረጫ መስፈርት ሊዘጋጅና በተዘጋጀው መምረጫ መስፈርት መሰረት ቴክኖሎጂዎችን የሚመርጥ ለየዘርፉ ኮሚቴ ከባለድርሻ አካላት ጋር

በመሆን በማቋቋም ቴክኖሎጂዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ በማድረግ ሽግግሩ እንዲከናወን የሚደረግበትን አሰራር ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

- በቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት ዙሪያ በሚከሰቱ ክፍተቶች ላይ ከባለድርሻ አካላት በጋራ በመሆን የሽግግሩ ሂደት የሚገመገሙበትና ክፍተቶች ተለይተው የሚሸፈኑበት ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ቴክኖሎጂዎችን ለማፈላለግ፣ ለመምረጥ፣ ለማስገባት፣ ለማላመድና ለማስወገድ የሚረዳ የግንዛቤ ማስጨበጫ ለባለድርሻ አካላት ሊሰጥና በጥናትና ዝግጅት ደረጃ ያሉ የግንዛቤ ማጨበጫ ፕሮግራሞችም ለህብረተሰቡ ተደራሽነት በሚሆንበት መልኩ ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችንም ሆነ በሀገር ውስጥ ኮፒ የተደረጉ ቴክኖሎጂዎችን ስለቴክኖሎጂዎቹ ለትምህርት፣ ለምርምር ተቋማትና ለሌሎች ተጠቃሚዎች በተለያዩ የማስታወቂያ ዘዴዎች በመጠቀም የማስተዋወቅ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡
- ለቴክኖሎጂ ሽግግር ወደ አገር ውስጥ ገብተው ጥቅም ላይ ሳይውሉ ወይንም በሥራ ላይ ተበላሽተው ያሉ ቴክኖሎጂዎችና ተጓዳኝ ዕቃዎች በባለሙያ ተረጋግጠውና ተለይተው ሰው፣ እንስሳትና አካባቢን በማይጎዱ መልኩ የሚከማቹበት እና የሚወገዱበት ሥርዓት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ቴክኖሎጂዎችን በአግባቡ ለማሸጋገር ሀገራዊ የቴክኖሎጂ አቅም መፍጠር ለማስቻል የተዘረጋው የትምህርት ስልጠና፣ የምርምር ተቋማት እና የኢንዱስትሪ ትስስር ለመፍጠር የተዘረጋው ስርዓት ተግባራዊነቱ ላይ ያጋጠሙ ችግሮችን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በጥልቀት ሊፈትሽና የመፍትሔ አቅጣጫ ሊያስቀምጥ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ከተለያዩ የትምህርት ተቋማት ተማሪዎችና አስተማሪዎች ያላቸውን ዕውቀት በተግባር ለመፈፀም ወደ ተለያዩ የኢንዱስትሪ ተቋማት በሚሄዱበት ወቅት ተገቢውን ዕውቀት ይዘው እንዲወጡ የሚደረግበት መንገድ ትኩረት ተሰጥቶት ክትትልና ድጋፍ ተደርጎበት ተገቢውን ዕውቀት ይዘው እንዲወጡ የሚደረግት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡
- ችግር ፈቺ ተብለው ከፍተኛ ወጪ ወጥቶባቸው የሚከናወኑ የምርምር ሥራዎች ወደ ተግባር የሚሸጋገሩበት ስርዓት በመዘርጋትና ተግባር ላይ እንዲወጡ

በማድረግ ሥራ ላይ እንዲውሉ በማድረግ ለምርምሩ መነሻ የነበሩት ችግሮች የሚፈቱበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡ በተጨማሪም በምርምር የተደረሰባቸው፣ የፈለቁ ወይም የተቀዱ ቴክኖሎጂዎች ወደ ምርትና ምርታማነት ለመቀየር የሚያስችሉ የቴክኖሎጂ ማበልፀጊያ ማዕከላትን በማቋቋም ምርምሮቹ ወደ ተግባር ተቀይረው ለባለድርሻ አካላት እና ለተጠቃሚዎች የሚሰራጩበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

- በሚኒስቴር መ/ቤቱ የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት መረጃዎችን ለመያዝ የተጀመረው በቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ አያያዝ ስርዓት ተጠናክሮ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችና ኮፒ የተደረጉ ቴክኖሎጂዎች ጭምር በማካተትና በማደራጀት ሊያዙና ለተጠቃሚው ህብረተሰብ የሚደርስበት ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፡፡ አገር በቀል የቴክኖሎጂ መረጃዎች በሚኒስቴር መ/ቤቱ ድረ-ገፅ ላይ እንዲቀመጡና ለህዝብ እንዲደርሱ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- በየዘርፉ የቴክኖሎጂዎች ፍላጎትን ለመዳሰስ፣ ለማፈላለግ፣ ለመምረጥ፣ ለማስገባት፣ ለመቀመርና ለመጠቀም ለማስወገድ የሚያስችል ስርዓት ከሚመለከታቸው ዘርፎች እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ሚኒስቴር መ/ቤቱ በመዘርጋት ዘላቂነት ያለው የቴክኖሎጂ ሽግግር ሥርዓት እንዲኖር ሊያደረግ ይገባል፡፡
- የሳይንስና ቴክሎጂን በባለቤትነት የሚያከናውኑ አደረጃጀቶች በሌላቸው ክልሎች ከየክልሉ መስተዳደሮች ጋር በመሆን አደረጃጀቶቹ የሚፈጠርበትን የቴክኖሎጂ ሽግግሩ የሚሳለጥበት ሁኔታ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሊያመቻች ይገባል፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ፣ የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ፣ የአዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት፣ ለኢትዮጵያ ቆዳ ልማት ኢንስቲትዮት፣ ለኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፣ ለኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ኃላፊዎች እና ለፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲና ለአዲስ አበባ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ቢሮ እና በናሙና የታዩ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

## አባሪ 1፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶችና ዘዴዎች

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (*Evaluative Criteria*) |
|---|---|
| 1. ቴክኖሎጂዎችን የማፈላለግ፣ የመምረጥ እና የማስገባት ስራዎች አፈፃፀም ወጪ ቆጣቢና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፣ | 1. ሚ/ቴር መ/ቤቱ ቴክኖሎጂዎችን ለማፈላለግ፣ ለመምረጥ እና ለማስገባት እንዲያስችለው አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያዎች ሊያወጣና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- 2ኛ ስትራቴጂ/2008-2012/ ዕቅድ ገፅ 4** |
| | *2.* ሚ/ር መ/ቤቱ የቴክኖሎጂ ሽግግርን በተመለከተ ልማታዊ እንቅስቃሴዎችንና ሀገራዊ የምርምር ፕሮግራሞችን ሊያስተባበር እና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ **ምንጭ- የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚንስቴር አዋጅ ቁጥር 691/2003 በ አዋጅ ቁጥር 916/2008 ቁ.4 እንደተሸሻለ** |
| | 3. ሚ/ር መ/ቤቱ የሀገሪቱን የቴክኖሎጂ ፍላጎትና ክፍተት መሰረት ያደረገና ሊሸጋገሩ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን በጥናት ላይ ተመስርቶ ሊያፈላልግ ይገባል፡፡ **ምንጭ- የሳይንስ ቴክኖሎጂ ኢኖቬሽን ፖሊሲ ማስፈፀሚያ ገፅ-4፣ የቴክ.ሽግግር ዳይሬክቶሬት የ2007 የ9ወር አፈፃፀም ገፅ 9/** |
| | 4. ሚ/ቴር መ/ቤቱ ከቴክኖሎጂ ሽግግር ጋር በተያያዘ በረቂቅ ደረጃ በማዘጋጀት ላይ ያለውን አገራዊ የቴክኖሎጂ አቅም ግንባታ ፍኖተ ካርታ በማጠናቀቅ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- የሚ/ር መ/ቤቱ የ2009 ግማሽ ዓመት አፈፃፀም ሪፖርት ገፅ 21/** |
| | 5. ሚ/ቴር መ/ቤቱ በየዘርፉ ሊሸጋገሩ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን ለመምረጥ የሚያስችል የመምረጫ መስፈርት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሊያዘጋጅና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- መልካም ተሞክሮ** |
| | 6. አዳዲስ የሚሸጋገሩ ቴክኖሎጂዎችን በመምረጫው መስፈርት መሰረት በየዘርፉ የሚመርጥና የሚገመግም ኮሚቴ ማቋቋም ይኖርበታል፡ **ምንጭ፡- መልካም ተሞክሮ** |
| | 7. ሚ/ቴር መ/ቤቱ በየዘርፉ እንዲሸጋገሩ የተመረጡ ቴክኖሎጂዎችን በመምረጫው መስፈርት በመምረጥ ተግባራዊ የሚሆኑበትን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡-መልካም ተሞክሮ** |
| | 8. በቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት ዙሪያ በየዘርፉ የሚከሰቱ ክፍተቶች በየሦስት ወሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ሊገመገሙ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- የሚ/ር** |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (*Evaluative Criteria*) |
|---|---|
| | **መ/ቤቱ የ2009 ግማሽ ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ገፅ 30/** |
| | 9. በቴክኖሎጂ ሽግግር የሴቶችን ተሳትፎ ተጠቃሚነት ባገነዘበ መልኩ ሚ/ር መ/ቤቱ ሊሰራ ይገባል፡፡ **ምንጭ የ2009 ግማሽ ዓመት አፈፃፀም ገፅ 9/** |
| 2.ቴክኖሎጂዎችን የማላመድ፣ የመጠቀም እና የማስወገድ ስራዎችን አፈፃፀም ወጪ ቆጣቢና ውጤታማ መሆኑን መገምገም | 10.ሚ/ቴር መ/ቤቱ በአገሪቱ ውስጥ ቴክኖሎጂዎችን ለማላመድ፣ ለመጠቀም እና ለማስወገድ የሚረዱ ሕጎችና መመሪያዎች እንዲወጡ በማድረግ ሥራ ላይ እንዲውሉ ሊያደርግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- መልካም ተሞክሮ** |
| | 11. ሚ/ቴር መ/ቤቱ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለማላመድና ለመጠቀም ወጥ የሆነና በዕቅድ የተያዘ የግንዛቤ ማስጨበጫ መረሀ ግብር በማውጣት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- መልካም ተሞክሮ** |
| | 12. ሚ/ቴር መ/ቤቱ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ተደራሽና ተደማጭ በሆኑ በማስታወቂያ ዘዴዎች ለህብረተሰቡ ሊያስተዋውቅ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- መልካም ተሞክሮ** |
| | 13.አዳዲስ አገልግሎት የማይሰጡ ቴክኖሎጂዎችም ሆኑ አገልግሎት ሰጥተው ተበላሽተው የተቀመጡት በባለሙያ ተረጋግጠውና ተለይተው በአግባቡ ሊወገዱ የሚችልበት ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- የሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ ማስፈፀሚያ ገፅ 5** |
| | 14.ቴክኖሎጂዎች በአግባቡ ለማሸጋገር ሀገራዊ የቴክኖሎጂ አቅም መፍጠር የሚያስችል ስርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- የ2009 ዓ.ም ዕቅድ ገፅ 7/** |
| | 15.አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለመቅዳት ወይም ለማላመድ እንዲያስችል ለየዘርፉ (ለባለድርሻ አካላት) ድጋፍ የሚደረግበት አሰራር ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፣**(ከ2008-2012 **የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ** 2 **ገፅ** 8) |
| | 16.በቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት ዙሪያ ለሚነሱ ቅሬታዎችን ፈጣን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡ መልካም ተሞክሮ** |
| | 17.የኢንዱስትሪ ተቋማት ቴክኖሎጂዎችን በጥራት በመቅዳት ወደ ኢንዱስትሪው የሚያስተላልፉበት የእርስ በርስ ትስስር ሊፈጠርላቸው ይገባል፡፡ **ምንጭ፡-** |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (*Evaluative Criteria*) |
|---|---|
| | **(ከ2008-2012 የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ገፅ 26፣ የሚ/ር መ/ቤቱ 916/2008 አዋጅ ቁጥር 6)** |
| | 18. በከፍተኛ ምርምር ተቋማት የሚከናወኑ ምርምሮችና ጥናቶች ወደ ተግባር የሚሸጋገሩበትን ሥርዓት ሚ/ር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡ **ምንጭ፡- መልካም ተሞክሮ/** |
| 3. በቴክኖሎጂ የተደገፈ መረጃ አያያዝ እና ከባለድርሻ አካለት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩን መገምገም | 19. በሚ/ር መ/ቤቱ በመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች፣ በከፍተኛ ትምዕርት እና በምርምር ተቋማት ጠንካራ የቴክኖሎጂ ሽግግር መረጃ አያያዝ ስርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ **ምንጭ-የሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂ ገፅ-8** |
| | 20. አግባብነት ያላቸውና ዕሴት የሚጨምሩ ለቴክኖሎጂ ሽግግር በግብዓትነት የሚያገለግሉ የቴክኖሎጂ መረጃዎችን በማደራጀትና በመተንተን ሊያዙና ለሚመለከታቸው አካላት ሊተላለፉ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- የሚ/ርሩ አዋጅ 916/2008 ቁጥር 12፣ የ2009 ግማሽ ዓመት አፈፃፀም ገፅ 31/** |
| | 21. ከባለድርሻ አካላት ጋር የመረጃ ልውውጥ የሚናበብ/የተጣጣመ እንዲሆን የሚያስፈልጉ የተለያዩ የመረጃ ማሰባሰቢያ፣ ማደራጃና ማሰራጫ ስታንዳርድ ፎርማቶች ሊዘጋጁና ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- የፖሊሲ ማስፈፀሚያ ትንሺ ገፅ 13/** |
| | 22. በየዘርፉ በሽግግር የሚመጡ ቴክኖሎጂዎችን መረጃ የመመዝገብ፣ የማሻሻል (ሞዲፋይ) የማድረግ፣ የማቀብና ለቀጣይ ስራ እንቅስቃሴም ሥራ ላይ እንዲውል የሚደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡ **ምንጭ፡- የሚ/ርሩ አዋጅ 916/2008 ቁጥር 3 እና የ2009 ግማሽ ዓመት አፈፃፀም ገፅ 59/** |
| | 23. ሚ/ቴር መ/ቤቱ ብሄራዊ የሆነ የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከል በማቋቋም ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- (የሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ** 17) |
| | 24. ትኩረት በተሰጣቸው የቴክኖሎጂ ዘርፎች የሚያስፈልጉ መረጃዎችን መለየት፣ በማዕከል ማሰባሰብ፣ ማደራጀት፣ መተንተን እና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማሰራጨት አለበት፡፡ **ምንጭ- የሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂ ገፅ-8** |
| | 25. ከተለያዩ መረጃ ምንጮች መረጃ ለማግኘትና የመረጃ |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (*Evaluative Criteria*) |
|---|---|
| | ልውውጥ ለማድረግ የሚያስችል የመረጃ ልውውጥ መሰረተ ልማት (ኔትወርክ) በማደራጀት ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡ **ምንጭ፡-የሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂ ገፅ-8** |
| | 26.የአገሪቱን የቴክኖሎጂ ፍላጎትን ለመዳሰስ፣ ለማፈላለግ፣ ለመምረጥ፣ ለማስገባት፣ ለመቀመር፣ ለመጠቀምና ለማስወገድ የሚያስችል ስርዓት ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ሊዘረጋ፣ ተግባራዊ ሊደረግና አፈፃፀሙን ሊከታተል ይገባል፡፡ **ምንጭ፡-የሚ/ርሩ አዋጅ 916/2008 ቁጥ 2፣ 2ኛስትራቴጂ ዕቅድ ገፅ 59/** |
| | 27.የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማትን ለማሳደግ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የቴክኖሎጂ ፍላጎትን መለየት ይኖርበታል፡ **ምንጭ፡-የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚንስቴር አዋጅ ቁጥር 916/2008 እና 2ኛ የዕትዕ ገፅ 8/** |
| | 28.ከባለድርሻ አካላት ጋር ለቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት እንቅስቃሴ የሚያግዝ ምቹ የርስበርስ ትስስርና ቅንጅታዊ አሠራር እንዲፈጠር የትስስር መድረክ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡- አዋጅ** 916/2008፣ 2ኛ **የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ገፅ** 22) |
| | 29.የግሉ ዘርፍ የቴክኖሎጂ ሽግግር ሥራዎችን በማከናወን እና በመደገፍ ረገድ ያለው ሚና በቀጣይነት እያደገ እንዲሄድ ለማድረግ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠር አለበት፡፡ **ምንጭ፡- የ2009 ዓ.ም ዕቅድ ገፅ 8/** |
| | 30.የዩንቨርስቲ መምህራን በየሙያ ዘርፋቸው በማምረቻና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ውስጥ በሚፈፀሙ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራዎች ውስጥ ቀጥተኛ ተሳትፎ እንዲኖራቸው የሚደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡-የሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂ ገፅ-31** |
| | 31.ዩንቨርስቲዎችና የመንግስት የምርምር ተቋማት በየዘርፋቸው ከግሉ መካከለኛና ከፍተኛ ማምረቻና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ጋር በምርምርና በቴክኖሎጂ ሽግግር ዙሪያ ተቀናጅተው እንዲሰሩ የሚደረግበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ **ምንጭ-የሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂ ገፅ-5** |
| | 32. የትምህርትና ስልጠና ተቋማት መምህራንና ተማሪዎች ተግባራዊ የተደረገ የቴክኖሎጂ ሽግግር |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (*Evaluative Criteria*) |
|---|---|
| | ግንዛቤ እና ስልጠና የሚያገኙበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡-(የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ** 2 **ገፅ** 26) |
| | 33. አገር በቀል አዳዲስ የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት መረጃዎችና የምርምር ውጤቶችን በሚ/ር መ/ቤቱ ድረገፅ ላይ ሊቀመጡ ይገባል **ምንጭ፡-መልካም ተሞክሮ** |
| | 34.በክልሎች የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት አገልግሎት ለሚሰጡ ተቋማትን ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጡ ክትትልና ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡ **ምንጭ፡ የ**2008 **ዕቅድ ገፅ** 42 |

# አባሪ 2፡ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር አደረጃጀት

